# ይላላ ደነቦ

ከ

**አምሀ አስፋው**

ለ

**መሱ**

**የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።**

Copyright © 1995 Amha Asfaw

**ወገኖቼ** (My People) **እና የኢትዮጵያ ጥሪ** (Call of Ethiopia)
**የተባሉት የ ላንግስተን ሂውዝ ግጥሞች የህግ መብት።**
Copyright © 1994 by the Estate of Langston Hughes. permission granted by Harold Ober Associates Incorporated.

**ሽፋን፡ አምሳለ አስፋው (መሱ) የእድገት በህብረት ልብስ ለብሳ።**

## ማውጫ


፯ መግቢያ

### ክፍል አንድ (አሜሪካ)

፲፫ ሚሲስ ፎርድ
፲፬ ክረምት
፲፭ ምእራባዊ ስልጣኔ
፲፮ ምክንያት
፲፯ መስተዋት
፳ ሰይጣናዊ ስንኞች
፳፩ ጭዳ
፳፫ የተረበሸ ፀጥታ
፳፬ ላኮታ
፳፭ የትምህርት ክፋቱ
፳፯ ጣእም
፳፰ ይበቃኛል
፳፱ ባርያ
፴ የጋን መብራት
፴፩ መቀመቅ
፴፫ ቦሎቄ
፴፬ በደም የተበከለ የፀደይ ሽታ
፴፰ እርግማን
፴፱ መንግስቱ ሀይለ ማርያም
፵ ደስታ
፵፩ እግዚኦ!
፵፪ ዝምታ
፵፫ አዋሽ

፵፬ ቃል
፵፮ ምእራብ ቨርጂኒያ
፵፯ ቀፎ
፵፰ ኮሎራዶ
፶ ቀለም
፶፩ የጎሳ ዴሞክራሲ
፶፫ ይገርመኛል
፶፬ መሱ

## ክፍል ሁለት (ኢትዮጵያ)

፶፰ ይላላ ደነቦ
፷፩ እውነት አትለካም
፷፪ ጠብታ
፷፫ መደነቅ ይሉኝታ ነው
፷፬ ምን ቸገረህ
፷፮ ልወቀው
፷፯ እስቲ አስቡት
፸ ከሰውነት ወደእቃ
፸፪ አማራ
፸፫ እውነት መሰል ውበት
፸፬ መፅሀፍ ቅዱስ
፸፮ ሌብነት ሲደነቅ
፸፯ ፍላጎቴ
፸፰ ጉራ
፸፱ ምን ያደርግላቸዋል?
፹ ንክች
፹፩ ስልጣኔ ያልሻረው ችግር
፹፪ የእውቀት መለኪያ
፹፫ በተስፋ ቢደሰቱ

፹፬ እርሻ
፹፯ ውበት
፺፪ እቃ
፺፫ ህልም ቢሆን
፺፬ ህይወት ሰው አትንቅም
፺፭ ውሸታሞች
፺፮ ዝናብ
፺፰ ዋይታ
፺፱ እውነተኛ ስቃይ
፻ ውሸት
፻፪ ጊዜ ሲቆም
፻፬ የዘመኑ ህብስተ መና
፻፭ ባለሁበት የማልገኝ
፻፯ ከእውነት ይሆን ስህተቱ?
፻፰ ኪነት
፻፲፩ አባሪ

# መግቢያ

ይላላ ደነቦ ለመታተም ከተዘጋጀ ረጅም ጊዜ ሆኖታል፡፡ ግን ሳይታተም እስካሁን ቆየ፡፡ በመሀሉም አድራሻየ ተቀየረ፣ ተጨማሪ ግጥሞች ተፃፉ፣ ቀደም ብለው የተፃፉት በከፊል ጠፉ፤ በቃል ተጠንተው የነበሩትም ተረሱ፡፡ ስለዚህ ይህች መፅሀፍ በሁለት ተከፈለች፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አሜሪካ ከመጣሁ በሁዋላ የተገጠሙ ወይም ጠፍተው፣ ተረስተው ከተረፈው ትውስታ እንደገና የተፃፉ ሲሆን፣ ኢትየጵያ በሚለው በሁለተኛው ክፍል የተመደቡት ደግሞ፣ ኢትያጵያ ሆኜ የፃፍኩዋቸው፣ አንዳንድ ለውጥ ባደርግባቸውም የለውጡ ምክንያት ፍላጎት እንጅ የመጀመሪያው ፅሁፍ መጥፋት ያልሆኑት ናቸው፡፡ በመፅ1ሀፉ መጨረሻ ላይ ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ግጥሞች የተዘጋጀ አባሪ ስላለ፣ ለውጦች ለምን እንደተደረጉ ለመረዳት ወይም ያልተለመዱ ቃላትን ትርጉም ለማወቅ ከዚያ መመልከት ይቻላል፡፡

የአቶ ሀዲስ አለማየሁን አርአያነት በመከተል፣ ተደጋጋሚ ፊደሎችን ከመጠቀም ተቆጥቤአለሁ፡፡ ሆኖም፣ ቀኃሥ የሚለው ምህፃረ ቃል፣ ከፊደልነቱ ይልቅ ወደ ስእላዊ ምልክትነቱ ስለሚያዘነብል፣ እንዳለ ትቼዋለሁ፡፡ በተጨማሪም «ሀ» እና «አ» ድምፃቸው ራብእ እንጅ ግእዝ ስላልሆነ ወደ ራብእነት ተዛውረው በፋንታቸው «ኸ» እና «ኧ» ተተክተዋል፡፡ ስለዚህ የ «ኸ» እና የ «ኧ» ዘሮች የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኸ | ሁ | ሂ | ሀ | ሄ | ህ | ሆ |
| ኧ | ኡ | ኢ | አ | ኤ | እ | ኦ |

የመጀመሪያ መፅሀፌ ስለሆነ ብዙ ወሬ አላበዛም፡፡ ግን፣ ልጠቅሰው የምፈለገው አንድ ሌላ ጉዳይ አለ፡፡

ኢትዮጵያውያን ከራሳችንና ከወገኖቻችን ስነ ፅሁፍ ይልቅ የፈረንጆችን ማንበብና ማድነቅ እናዘወትራለን፡፡ ይህ ጠባያችን ኩሩነታችንን እየቀነሰ፣ የበታችነት ስሜታችንን እያካበተ ኖሮ አሁን ከወደቅንበት አዘቅት ውስጥ አድርሶናል፡፡ የጥቁር ህዝቦችን ስራ የራሳችን፣ ታሪካቸውን ታሪካችን፣ ምኞታቸውን ምኞታችን አድርገን መቀበል አለብን፡፡ እነሱ በኛ እንደኮሩ ሁሉ እኛም በነሱ ስራ መኩራት ይኖርብናል፡፡ ከፑሽኪን ይልቅ፣ ላንግስተን ሂውዝ፣ ከ ሼክስፒር ደግሞ ኮንቲ ኩለን ይቀርቡናል፤ ስሜታችን ይሰማቸዋል፣ ስሜታቸው ይሰማናልና፡፡

እዚህ አሜሪካኖች የሚያዘወትሩት አንድ አባባል አለ፤ «You know what I mean» ይላሉ፤ የልባቸውን ለማውጣት ቃል ሲቸግራቸው፡፡ እኔም፤ ለማለት የፈለግሁት እንደገባችሁ በማመን፣ ላንግስተን ሂውዝ የተባለ ጥቁር አሜሪካዊ ደራሲ ስለኢትየጵያ የፃፈውን ግጥም ላስከትልላችሁ፡፡ የሚቀጥለው መፅሀፌ የዚህ ታላቅ ሰው ግጥሞች ትርጉም ሳይሆን አይቀርምና፣ ላንግስተን ሂውዝን በዚህ አጋጣሚ ከኢትዮጵያውያን ጋር ማስተዋወቄ አይከፋም፡፡

# የኢትዮጵያ ጥሪ

ኢትዮጵያ፣
አቅኝ ፊትሽን፣ ጥቁሩን ጨለማ፤
    አበሻ፣
    የሳባ ልጅ ዝርያ !
    ዘንባቦችሽ ረጃጅም፣
    ተራሮችሽ የመጠቁ፣
    መጠለያ ናቸው ጋሻ፣
    ለነፃነት ሲሉ ለሚወድቁ-
    በመስዋ»ትነትሽ ፈለግ ፣
    መላው አፍሪቃ ይነሳ፤
    አይኑ እሳት ጎርሶ፤
    ፊቱ ድቅድቅ ጨለማን ለብሶ፣
    የሳባን ዘር ጥሪ ሰምቶ፥

    ነፃ ናት ኢትዮጵያ!
    እናንተም ሁኑ እንዲያ፣
    መላው አፍሪቃ፣
    ተነሱና ሁኑ ነፃ!
    የጥቁር ህዝቦች ሁሉ፣
    ሁኑ ነፃ! ሁኑ ነፃ!

ላንግስተን ሂውዝ፡፡
መስከረም ፲፱፻፴፰ ኢ.ም (እንደ ፈረንጅ አቆጣጠር)፡፡
ትርጉም፥ አምሀ አስፋው፡፡

## ክፍል አንድ

# አሜሪካ

# ሚስስ ፎርድ

አያት ቅም አያቶችዋ
የተወለዱበትን፣
እትብታቸው የተቀበረበት
እትብትዋ የተቀበረበትን፣
አገርዋን፤

ስትናገር የሚገባቸው
ሲናገሩ ሚገባትን፣
ቀልድዋ የሚያስቃቸው
ቀልዳቸው ደግሞ ሚያስቃትን፣
ወገኖችዋን፤
ትታ፤

አልገዛም አሻፈረኝ
አልሆንም ባርያ ለነጭ ዘር፣
የማይበገሩ ዘመዶች እያሉኝ
ከባህር ማዶ ባሻገር፣
ብላ፤

ከሌላው ምድር ሁሉ
የኔን ሀገር መምረጥዋ፣
ከሌላው ደንቆሮ ሁሉ
እኔን ማስተማር መፈለግዋ፣
ሊገባኝ አልቻለም ነበር፤
የመውደድዋ ምልክት መሆኑ፣
የፍቅርዋ።።

# ክረምት

አረንጉዋዴ ሆኖ፣
ህይወት መስሎ፣
ህይወት ለብሶ፣
ቅጠል ሸፍኖት፣ አምሮበት፣
የነበረው ዛፍ እንደትናንት፤

ዛሬ ቅጠሉ ረግፎ፣
ግንዱ እርቃኑን ቀርቶ፣
በደም ስሩ የቆመ ሽማግሌ ይመስላል፣
ስጋው ተሙዋጦ አልቆ።

ኑረታው ያከተመ፣
የሞተ ያለቀለት፣
የማይለመልም ተመልሶ፣
አብቦ ማያምርበት፣
ይመስላል ለተመልካች፣
ይሄ ክረምት ሲያልፍለት።

፲፭

# ምእራባዊ ስልጣኔ

ዋናው ነገር፣
አለማስቀየም ነው፣
አሜሪካን፣
እንግሊዝን፣
እስራኤልን።

እነዚህን፣
የዴሞክራሲ ጠባቂዎች፣
የእውነት ደንጋጊዎች፣
እስካላስቆጣህ፣
እስካላስከፋህ፤
ትንሽ ጠመንጃ ፈልገህ፣
እስዋን እየተኮስክ፣
እየተኩዋኮስክ፣
አራት ኪሎ ትደርስና፣
እንደምንም ብለህ፣
ርእሰ-ብሄር መሆን ነው፤
ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሂደህ።

ምን ይፈይዳል ብለህ ነው ድሮስ፣
የተለዬ፤
ይሄው ነው ዴሞክራሲ፣
ምእራባዊ ስልጣኔ፤

ይሄው ነው።

፲፮

# ምክንያት

ትንሽ ምክንያት ይበቃል፤
እርምን ለማውጣት፣
ፍቅርን ለመቅበር፤
አንጀት ለመቁረጥ ለመጥላት፣
ለማለት አይንህ ላፈር፣
ለማለት አይንሽ ላፈር፤
ትንሽ ምክንያት ይበቃል።

# መስተዋት

በርጫ እንቀመጥና፣
ጫት ቅመን ስንመረቅን፣
የማርክስ ደቀ መዝሙሮች ይጀምራሉ፣
ያንን የማያልቅ ክርክር፡፡

*«እኛ ግዙፍ አካል ነን፣ የተለካ ዋዘፎአችን፣*
*ሰውነታችን የታወቀ፣ የተረገጠ ኑረታችን፡፡»*

ይላሉ፡፡

እኔም፣

ጫቴን ጎስሬ በጉንጬ
ኒያላየን በረጅሙ ስቤ፣
መጥጬ
ቁሩዬን አጠገቤ ላለው ፈላስፋ፣
አሳልፌ ሰጥቼ፣

*«እስቲ ስነ-ፍጥረታዊ ፍትሽት ስሩ፤*
*ቆማችሁ ከመስተዋት፣*
*መሆኑን የሚያሳይ በርግጥ፣*
*የናንተ አካል እውነት፣*
*ምስላችሁ ግን የሀሰት ቅርፅ ፣*
*አእምሮ የፈጠረው ህስበት ?»*

እላለሁ፡፡

፲፰

ይሞክራሉ ሊያስረዱኝ፣
መስተዋት ፊት እንቆምና፣
ሳያወላውል እንደሚገዋዝ፣
ብርሀን፣
መስመር ተከትሎ በቀጥታ፤
ሲመታ ብርሀኑ መስተዋቱን፤
ወይም ነፀብርቃው ሲመለስ፣
ከመስተዋቱ ገን ጋር የሚፈጠረው ዘዌ፣
በሂሳባዊ መልኩ ሲገለፅ..........።

ከዚያም ይጠይቁኛል እንድነካቸው፣
እንድረዳ፣ የሰውነታቸውን ጥጥርነት፣
አያውቁትም ልበል፣ ወይ ይዘነጉታል፣
ድንቢጥ፣ እንደማትሆን ምስክር ለአይጥ።

ይህ ሁሉ ሲሆን፣
ስነ-በሲር በየመልኩ ሲነጠፍ፣
ሂሳብ በየፈርጁ ሲረግፍ፣
ፊዚካ ሲመነዘር፣
ጥልቅ ሚስጥሩ ሲለፈፍ፤

እኒያ ሁለት እንትኖች፣
ከመስተዋቱ ውስጥ የቆሙ፣
እኛ ምስል የምንላቸው፣
እነሱ ግን እኛን የሚሉ፣
ቀኙን እንደግራ፣
ግራውን እንደቀኝ የሚቆጥሩ፣

## ፲፱

ይከራከራሉ ቆመው፣
ኑረታቸውን ለማወቅ፣
የኛን ምስልነት ለመመስከር፣
የኛን ምንም-ነት ለማፅደቅ፡፡

ማንኛችን ነን ጥጥር?
ማንኛችን ነን እውነት?
ማንኛችን ነን ህያው?
ማንኛችን ነን ህስበት?

እስቲ ፍትሸት ስሩ፣
ከመስተዋት ቆማችሁ፣
የናንተን ታላቅነት የሚያበስር፣
የማይችሉት ምስሎቻችሁ፤

እንያችሁ፡፡

፳

# ሰይጣናዊ ስንኞች

የንግግር ነፃነት፣
የውሸት መድረክ መሆን የለበትም፤
የገንዘብ ማካበቻ ልቂት፡፡

ነፃነት፣
የነጭ ዘረኞች መፈንጫ፣
ከሆነማ የበላይነት ስሜታቸውን መወጫ፣
ምን አርግ ትሉታላችሁ ሆሜኒን?
በደነገገ ነፃነቱን፣
ባሰራጨ ውሸቱን፣
ምን አርግ ትሉታላችሁ?

ውሸት እውነት ይሆናል አሉ፣
ለነጭ ህሊና ከጣመ፣
እኛ አሜን ብለን ተቀብለናል ፣
ወኔያችን ስለደከመ፡፡

ለታላቁ ሆሜኒ ግን፣
እውነት የራሱን ድንጋጌ ካላቀፈ፣
የወገኑን ህሊና ካልጣፈ፣
ወይ ድንጋጌው ይጠፋል፣
ካልሆነም ደንጋጊው ይቀሰፋል፣
ያልፋል፤
ያንቀላፋል፡፡

መልካም እንቅልፍ፤ ረሽዲ!!

## ጭዳ (ለተፈሪ ቦጋለ)

ደክሞት፣ አማርኛ ሲያስተምር ውሎ፣
ከቴጌ መነን ኮረዶች ጋር፣ ተጨቃጭቆ ተዳርቆ፣
ይመጣና ከቤቱ፣ የሚታረም ወረቀት ተሸክሞ፣
ከምግብ ቤቱ ወንበር ላይ ይቀመጣል፤
        አይኑን ጨፍኖ ተንጋሎ።

እንዲያ አይኑን ጨፍኖ፣ ትንፋሹ ሲመለስለት፣
ወንበሩን ባራት እግሩ ያሳርፈዋል፣
                መልሶ ከተንጋለለበት።
ከዚያም፣ ከጠረቤዛው ላይ፣
                አንዱን የተማሪውን ወረቀት ያነሳና፣
አንብቦ ወደጎን ያስቀምጠዋል፣ በእግሩ ሌላ ይተካና።

የሚያነበው ካልጣመው፣ ይሰበስባል ከንፈሩን ወደቀኝ፣
ወይ ይስቃል፣ ፅሁፉ  ከሆነበት የልጅ ነገር የሞኝ፤
አንዳንዴ ግን ፊቱ፣ በደስታ ይሞላል በፈገግታ፣
ያነበበውን ሲወደው፣ የቀን ድካሙን ሲረሳ፤
በተማሪው ግጥም ሲረካ፣ ባስተማሪነቱ ሲኮራ።

ስማ አምሀ! ይለኛል እንዳጋጣሚ ካለሁ እዚያ፤
ስማ አምሀ . . . . . . . . . .

*«የትም ስዞር እውልና፣*
        *አልጋየ ላይ ጋደም ስል፣*
  *ስለነገ ማሰብ እጀምራለሁ፣*
        *ደህና ማደሬን አውቅ ይመስል።»*

ትላለች፤ የተፈሪ ተማሪ የመነን፣
ያላየሁት ፊትዋን፣ የማላውቀው ስምዋን።

አንድ ቀውጢ ቀን፣ ቀይ ሽብር ነው ተባለና፣
ያች ትንግርተኛ ልጅ እንዳለችው፣
ተፈሪ የትም ሲዞር ውሎ፣ አልጋው ላይ ይጋደምና፣
ስለነገ ያስብና፣ ለልጆቹ ይመኝና፤
ይተኛል ሰውነቱን ሊያሳርፍ፣ ድካሙን ሊወጣ፣
የዘለአለም እረፍት መቃረቡን ሳያውቅ፣
                የዘለአለም መኝታ።

        *«ወዮላቸው ለነዚያ፣*
                *ያላወቁትን ለማሳወቅ ለሚጥሩ፤*
        *ማዘንስ ለነሱ ነው።*
        *በእንቅልፍ ልቡ ሞተ፣*
        *የሚሉት ተረት፣*
                *በቦሪስ ፓስተርናክ ተጀመረ።»*

ይል ነበር፣ ተፈሪ፣
የራሱን ግጥም ሲያነብ ይሆን እንጃ፣
                ወይ የቴጌ መነን ተማሪ።

አልታደለም ተፈሪ፣ እንደፓስተርናክ፣
በእንቅልፍ ልቡ ለማረፍ፣ በእንቅልፍ ልቡ ለመሞት፣
አልታደለም።

አማምዋቱን ልተወው፣
                ምን ያደርጋል አማምዋቱ፣
የቀይ ሽብር ጭዳ ሆነ፤
                አይበቃ ይሆን ማለቱ?

፳፫

# የተረበሸ ፀጥታ

ጠፋብኝ ግጥሜ፣
ምስጋናዬ፣
ዝማሬዬ፤
ጠፋብኝ ብስጭቴ፣
እሮሮዬ፣
ምሬቴ፤
የምለው ነገር አጣሁ፣
የምመኘው፣
የማወግዘው፤
ሁሉም ነገር አለ ፀጥ፣
ሞገድ እንዳልሆነ ክትለቱ፣
እርግብጋቦ፣ የባዶ ውስጥ።

እሪታው አያቆም፣
ጩኸቱ፣
የርግብግቢቱ፤
አይደርስም እንጅ ከሰው ጆሮ፣
ሞገድ ፈጥሮ፣
ባዶን አልፎ፤
አቸንፎ።

ሀፍረት ይሁን ንዴት፣
ሀዘን ይሁን ወይ ፍርሀት፤
ያልታወቀ ነገር ምንነቱ፣
እንግዳ ዱብ እዳ፤
የደፈረሰ ጥራት፣
የተረበሸ ፀጥታ።

# ላኮታ

እንሂድ፣
*ቤት?*
ላኮታ፣
*ለምን?*
ልንጠጣ፣
*ምን?*
ቡና፣
*የምን?*
የከፋ፣

*የከፋ!*
*ማለትህ ይሆን፣ ያስመራ?*
ያስመራ!
ይመረት ጀመር እንዴ፣ ቡና፣
በኤርትራ?

*እንዴታ!*
*ያውም የተጣራ የነጣ፤*
*ሲሉ አልሰማህም እንዴ፣ ፀአዳ፣*
*ነጭ ቡና ለነጭ ጌታ።*

፳፫

# የትምህርት ክፋቱ

ይሄ፣ ተረት ነው የአስፋው፣ ያባቴ፣
እሰማው የነበር ሁሌ፣

*፳ አመት አገር ምድሩን ሲያስስ፣*
*ኖሮ፣*
*በችግር ዳሽቆ፣*
*በረሀብ ተቆልቶ፣*
*በሸዋ፣ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎ፣*
*ተንከራቶ፣*
*ተምሮ ሲመለስ ወደቤቱ፣*
*ቀስሶ፤*
*ፊደል ከቆጠረበት በተስኪያን ደረሰ፣*
*ድሮ።*
*ካጥር ቆሞ፣ ተክዞ፣*
*እንባው ቀሮ፣ ፈዞ፤*

*ሳለ፣*
*ድምፅ ሰማ ከውስጥ፣ የልጅ፣*
*«ሀ» አለ ማሙሽ «ሁ» አለ።*

*አዳመጠና በሀዘን በትካዜ፣*
*«የትየለሌ!! »*
*አለ፤*
*«ማሙሽ የትየለሌ!!»*

## ፳፮

ይህ ደሞ ጭማሪ ነው የኔ፤

እንኩዋንስ ኮከብ ሊቆጥር፣
ጠፈር ሊመትር፤
          እኩልታ ሊመደብል፣
          ከስነ ዛመዶ ጋር ሊኮበልል፣
ሊነድፍ ይቅርና መቀምር፣
ሊፅፍለት መርሀ ግብር፤

አይነካትም ነበር ማሙሽ፤
                    ፈደልዋን፣
አይጠራም ነበር ስምዋን፣
                              የህን፣
                                 የሁን፤
ቢያውቅ እንዲህ ከፊቱ፤
የትምህርት ክፋቱ፣
          መሆኑን መሰልቾቱ።

# ጣእም

ከ ቀኃሥ ገዳመ-ጥበብ አንዴ፣
          ከ አራት ኪሎው ግቢ፤
አንድን፣
          የቅማሞ አስተማሪ፤
ብለው ጠየቁት ተማሮች፣
          «እስቲ እነዚህን ቅመስና፣
ንገረን የቱ እንደሚጣፍጥ፣
          አስተውለህ በጥሞና፡፡»

እሱም፣

«እንዴታ በደስታ፣
ግን አስረዱኝ እባካችሁ፣
          ሳልጀምር በፊት ቅምሻ፣
ምን ማለት እንደሁ መምረር፣
                    መኮምጠጥ፣
የጥሩ ጣእም ባለቤት መሆን፣
                    መጣፈጥ፣»
አላቸው፡፡

አልቻሉም ተማሮቹ ሊያስረዱ፤
እነሱም ወደሌላ ምላስ፣
          መምህሩም ሳይቀምስ ወደቤቱ፡፡

# ይበቃኛል

ዛሬ እየፈረሰ ነው፤
          እየተናደ፤
ነገም ሆነ፣
          የማልደርስበት ተስፋ የጨለመ፤
አልፈልግም ልለውጠው፣
ሳጠፋው፣ ልበርዘው፤
ትናንት፣ ነውና የኔ፣
ልጅነቴ።

ይበቃኛል ያካበትኩት፤
          ያጠራቀምኩት ትዝታዬ፣
ለተረፈው እድሜዬ፤
ይበቃኛል።

# ባርያ

ለብዙ ዘመናት ሲገዛ፣
ነጮች ሲገርፉት፣ ሲንቁት፤
ጥርሱን እየገለጠጠ፣
ከበደኝ ሳይል፣ ባርነት፤
ውሻ ሆኖ፣ ውሻ መስሎ፣
ጭራውን እየቆላ፣ አሜን ብሎ፣
ባርነቱን ተቀብሎ፣
ኖሮ፤

ይናፍቀዋል የጌታው ሀገር፣
ያኮራዋል የጌታው ስራ፣
ይመስለዋል የሰለጠነ፣
በጌታው ልሳን ሲያወራ፤
ይጥመዋል የጌታው ቀልድ፣
ያምረዋል የጌታው መልክ፣
ይተናነቀዋል እንባ፣
የጌታውን የህዝብ መዝሙር ሲሰማ፤

ደሞ፣
«ነፃነቴን ስጡኝ፤» ይላል አፍ አውጥቶ፣
ትርጉሙን ያውቅ ይመስል፣ ከቶ፡፡
ሌሎች መስዋእት ሆነው ያዳኑት ህዝብ፣
ያጎናፀፉት ነፃነቱን፤
የባርነቱ ዘመን ይናፍቀዋል፣
ለመሸፈን እፍረቱን፡፡

አይ ባርያ!

# የጋን መብራት

ራሳችሁን አታታሉ፣
          የጋን መብራት ነን ብላችሁ፤
የጋን መብራት ይበራል፡፡

ራሳችሁን አታታሉ፣
          የተዳፈንን ፍም ነን ብላችሁ፤
የተዳፈነ ፍም ይያያዛል፡፡

ራሳችሁን አታታሉ፣
          እሳታችን አልቆ የቀረን አመድ ነን ብላችሁ፤
አታውቁምና ነዳችሁ፡፡

የላችሁም መንደጃው፣
                    ቅባቱ፣
የብርሀን ሁሉ መሰረቱ፤

የላችሁም፡፡

# መቀመቅ

ቀኑን ሙሉ ውሎ ሲያካፋ፣
ማባራቱ ነው አሁን ገና፡፡
ፀሀይዋን ደመና ሸፍንዋት፣
        ጨልምዋል ሰማዩ፣
አይታወቀኝም እንጅ ለእኔ፣
        ሳይበርድ አይቀርም ውጩ፡፡

እኔ ግን እሳቴን አንድጄ፣
በሚወዛወዝ ወንበር ላይ ተቀምጬ
የከርሞ ሰውን አነባለሁ፣
        የአብየን ግጥም ገልጬ

ማንበብ ሰልችቶኝ፣
        አይኔን በመስኮት ሳቀና፣
ነጭ አጥር ይታየኛል፣
        ከጀርባው ለምለም ኮረብታ፣
ፈርከክ፣ ፈርከክ የሚሉ ላሞች፣
        ጡታቸው የከበዳቸው፣
ይታዩኛል ሲግጡ፣
        ደመናውን ተገን አርገው፡፡

ዋ!
የአብዬን ግጥም ለማድነቅ፣
ከዚህ የተሻለ ቦታ አልነበረም፣
        የጥቁር አፈርን ጣእም ለማወቅ፡፡

፴፪

ምኞቴ መበላሸቱ፣
ህልሜ ህልም ሆኖ መቅረቱ፣
ቢያላቅቃት ኖሮ አገሬን ከድህነት፣
ከልመና ከጦርነት፣
ባልከፋ ነበር መረገሜ፤
አድህሪ መባሌ።

ግን የገባንበት አዘቅት፣
አጥንት የሚሰብር ውርደት፤
የፈረንጅ መመፃደቂያ መሆን፣
አለም- አቀፍ ለማኝነት።
መቀመቅ።

ኧረ ምን ይሆን ባእሙ፣ የመኖር፤
እያሰቃዩ ሙሉ ሀገር።

# ቦሎቄ

ቦሎቄው ፈስዋል ከሜዳ፣
አልበቃ ብሎት ጎተራ፤
ነጋዴው ደጅ ይጠናል፣
ተኮልኩሎ በተራ፡፡

«ላንሳልዎት በሙሉ፣
ልስጥዎት በኩንታል ሰማንያ፣
አይሞኙ ጌታዬ፣
ይቆጭዎታል በሁዋላ፡፡ »
« ምን ሲደረግ!»
አሉ ጌታው፤
« ንክች አላደርጋትም፣
መቶ ካልሞላ ዋጋው፡፡»

ወራት አለፉ ሳይሸጥ፣
ቦሎቄ እንደፈሰሰ፣
ሰማዩም አጉረመረመ፤
ጥቁር ደመና ለበሰ፣
ዘነበ፣
ተተራመሰ፣

አይ ቦሎቄ .....
አለቀ እንግዴህ በሰበሰ፡፡

ከንቱ ልፋት፣
አለመጠን መንገብገብ፣
በታምር ለመክበር መነሳት፡፡

# በደም የተበከለ የፀደይ ሽታ

- ፩ -

ክረምት አልፎ ፀሀይ ሲወጣ፣
የቤት መስኮት ሲከፈት፣
የፀደይ ንፁህ አየር ሲገባ፣
የሚዙሪ የቅርጫት ኩዋስ ቡድን፣
ነብርነቱ ቀርቶ ቅሪላ ሲሆን መጫወቻ፣
የኮሎራዶ፣ የኦክሎሆማ፣ የአየዋ፣ ማላገጫ፣

ተደራርቦ ነው መሰል ይህ ሁሉ፣
የሌሊቱ አየር ሙቀቱ፣
የኩዋስ ጨዋታው ንዴቱ፣
ማለም ያበዛሁበት ጊዜ ነበር፣
ያዘወተረኝ ቅዠቱ፡፡

- ፪ -

በህልሜ ነው አንዴ፣
የማላስታውሳቸው ሰዎች፣ እናቴና እኔ፣
እናሳፍራለን ከመርከብ፣
በውሀ ውስጥ እየነዳን ፤
የሚተራመሱ በጎች፣
እየጎተትን እየገፋን፡፡

፴፫

ከበጎችዋ አንድዋ፣ ግልገልዋ፤
መሄድ ስላልቻለች በራስዋ፣
መዘዝኩና መጥረቢያዬን ከጎኔ፣
አራት እግርዋን ጣልኩላት አሽቀንጥሬ።

ከዚያም ግልገልዋን አንከብክቤ፣
ከመርከብ አሳፈርኩዋት፣ ውሀ እንዳይነካት ታቅፌ።
ለካ አይታ ኖሮ ይህን ጉድ እናቴ፣
«ምነው ምን ነካህ ልጄ፣
መላወስ መራመድ ካልቻለች፣
አትቆይም እኮ ብዙ፣ በረሀብ ትሞታለች፤»
ብላ ተቆጣች፤ አዘነች።

እኔም ተፀፀትኩ በድርጊቴ፣
እግርዋን በመቁረጤ፣ ማሳፈሬ ላይቀር ታቅፌ፤
«እባክሽ እማምዬ! ከምትሰቃይ እንዲህ ሆና፣»
ለመንኩ፤ «አርደን እንብላት አልኩና።»

- ፫ -

የልመናዬን ውጤት ሳልሰማ፣
ግልገልዋን አርጄ ሳልበላ፣
ብንን አልኩ ከእንቅልፌ፣
ሌሊቱ ሊነጋ ነበርና፣ አልቻልኩም ልተኛ ተመልሼ።

ይህ የቅዠት አለም፣ ይህ የቅዠት አንድምታ፣
ቅደም ተከተሉ አይሳካ፣ ተገላቢጦሽ ነው የውነታ።
መቆረጡ፣ የግልገልዋ አራት እግር፣
እንዴት ነበር የሚረዳት ባህሩን ለመሻገር?

እግር የሌለው በግ መራመድ የተሳነው፣
ያንዣብባል በአየር? ያርጋል ወደሰማይ?
ወይ ባህሩን ሰንጥቆ ያልፋል?
ይንሳፈፋል በውሀ ላይ?

«አላግዝም እግረኛ፤
አልታቀፍም ጤነኛ፤
የኔ እንባ ካሰኛችሁ፣
መሰቃየት መቸገር ምስኪን መሆን አለባችሁ፡፡»
እንዲያ ይሆን አንድምታው? እንዲያ ይሆን ሚስጥሩ?
የቅዠት ህልውናው፣ የቅዠት ውጥንቅጡ?

ግልፅ ያለ ነገር ቢኖር ፣ የማያሻማ ትርጉሙ፣
በግዋን ማረድ መፈለጌ ነበር፤ ስጋዋን ቀቅዬ መብላቱ፣
ያላቅቃልና ግልገልዋን፣ ከቀራት የስቃይ እድሜ፣
እኔንም ከራሴ መርገም፣ እኔንም ከጭንቀቴ፡፡

- ፩ -

ግን ይህ የውን አለም፣
በምን ይለያል ከቅዠት፣ በምን ይለያል ከህልም፥

ያፍሪቃ ህዝብ በራሱ፣
ያጠራጥራል  የዲሞክራሲን ስርአት ማንገሱ፣

ተብሎ፣

ነጮች ነፃነቱን እንዲገፉት፣
ሰውነቱን እንዲገርፉት፣
ህይወቱን እንዲያጠፉት፣
                    መስማማቱ፤
እግር ከመቁረጥ ጋር ምን ይሆን ልዩነቱ?

ፓናማን ወሮ፣
የምጣኔ-ሀብትዋን መዋቅር አበላሽቶ፣
በቢሊዮን የሚቆጠር የገንዘብ ምንጭዋን አጥፍቶ፣
የመቶ ሚሊዮን ብር እርዳታ መስጠቱ፤
የግልገልዋን እግር ቆርጦ፣
          ታቅፎ ከማሳፈር ምን ይሆን ልዩነቱ?

የአሜሪካን ጥቁር ህዝብ ንብረት እንዳያበጅ ከልክሎ፣
አይሞት ነገር በረሀብ፣ ምግብና ገንዘብ ተንጣሎ፣
ወይ ሰረቀ ወይም ገደለ ብሎ፣
እስር ቤት እንዲማቅቅ ማድረግ ከህብረሰቡ ተገሎ፤
ምንድነው ልዩነቱ፣
ግልገልዋን ገሎ ከመብላቱ?

፴፫

# እርግማን

ውለጅ ተባልሽ እንጅ፣
    ጥቁር ውሻ፤
ማን ረገመሽ፣
    እንድታጠቢ ባንዳ፤
የሚገዛሽ ሳይሆን ራሱ፣
    የሚሸጥሽ ለባዳ፡፡

፴፱

# መንግስቱ ሀይለ ማርያም

አርፈህ ጠጅህን እንዳትጠጣ፣
ከረምቦላህን እንዳትመታ፣
አገር እገዛ ብለህ
አየህ የመጣብህን ቁጣ!
አየህ ያመጣኸውን ጣጣ!
ከሚወዳት መሪ በቀር፣
ይህ ጎደላት 'ማይልዋት አገር፣
አረግሀት የአለም ህዝብ መሳቂያ፣
የምድረ አዝማሪ መሳለቂያ፡፡
ጥቁሮች ይኮሩባት የነበር፣
የነቴዎድሮስ፣ የነምኒልክ አገር፣
አረግሀት የለማኞች ምድር፣
ስምዋ ሲጠራ የሚያሳፍር፡፡
እስቲ ይመችህ እንደሆነ እናያለን
በነጮች አገር መኖሩ፣
አላፊ አግዳሚው ሲገላምጥህ
ሲንቅህ ውራውሩ፡፡

ይሻልህ ነበር ቢቀርብህ
አርፈህ ጠጅህን ብትጠጣ፣
ከረምቦላህን ብታምታታ፣
ይሻልህ ነበር ቢቀርብህ፣
ይሻለን ነበር ቢቀርብን፣
ከዘበኝነትህ ባትወጣ፡፡

፵

# ደስታ

የደስታ እስክስታ፣
ቢሆን ኖሮ ከአውሮጳ የመጣ፣
የኛ ልጆች፣
        ያስነኩት ነበር ጭፈራውን፣
ይህን ጊዜ፣
        እስክስታውን፡፡

ግን  ሆነና የኛው ጉድ፣
        ማን ንክች በግድ፣
        ማን ንክች በውድ፡፡

እንጀራ ሆኖባት ይሆን? ደስታ፣
አዶ ከቢር ይመስል፣
        የምትርገፈገፈው ጥዋት ማታ?

ያውሮጳን ዳንኪራ መርገጡ፣
        ቢሆንማ የመሰልጠን ምልክቱ፣
ከደስታ የተሻለ ማን ነበር፣
        ላራዳ ልጅነቱ?
የለም፤
የእንጀራ ጉዳይ ብቻስ አይደለም፡፡
በችሎታዋ ብታምን ነው፣
        በባህልዋ ብትኮራ፤
ራስዋን ለባርነት፣
        ባትሸጥ አሳልፋ፤
        ደስታ .....

# እግዚኦ!

የመረጡትን መርጦ፣
የረሱትን ረስቶ፣
        ትቶ፤
ጠላን ያሉትን ጠልቶ፣
ሆን ያሉትን ሆኖ፣
        መስሎ፣
        ተመስሎ፣
አለሁ ብሎ፣
        ተቀብሎ፣
እርሱ ተበድሎ፣
ለመኖር ሲል ግን አታሎ፤
አታሎ ይባል ይሆን? ተታሎ?
ብቻ ለመኖር ሲል መስሎ፤

እግዚኦ!

ህይወት ለምን እንዲህ ጣፈጠ?
        መኖር ምነው ዋጋው በዛ?
የልብን ውሳኔ እስኪጥስ፣
        ህልውናን እስኪገዛ፡፡

፵፪

# ዝምታ

ዝምታ ወርቅ ነው፣
          ይላል ያገሬ ሰው፣
ዝም፤ ባለ አፍ፣
            ዝምብ አይገባበትም፣
                        ይላል ያገሬ ሰው፣
አላዬ አሜሪካን፣
ዝምታ ስንፍና፣
          ዝም ያለ ደንቆሮ፣
                    የሆነበት አገር፡፡

፵፫

# አዋሽ

በልቻለሁ እንጀራ!

በአስራ ስምንተኛው መንገድ፣ በመናገሻው ከተማ፣
በቦስተን፣ በዳላስ፣ በፍሪስኮ፣ ባትላንታ፣

ኮሎራዶን ተንተርሼ፣ በረዶውን አይቼ፣
ከዴንቨር ላይ ተንጠልጥዬ፣ ሰማዩን ተጠግቼ፣
በልቻለሁ እንጀራ።

ካፌ ካሉች፣ መስከረም፣ አዲስአባ፣ ፋሲካ፣
ጥቁር አባይ፣ ካል ማርት፣ ሌላም ስሙ ማይጠራ፣
ስንቱን አየሁ እዚህ አገር፣ ስንቱን አየሁ አሜሪካ።

ግን አልበላሁም ባናቱ፣ አልቀመስኩም ሽፍንፍን፣
እንደ አዋሽ የሚጣፍጥ፣ እንደ አዋሽ የሚጥም።

፵፬

# ቃል

ማን ያውቃል፣
ይለወጥ ይሆናል ቃል፣
ወደሚጨበጥ አካል፡፡

አስማተኞች ሲደግሙ፣
መተታቸውን ሲያሰሙ፣
እቃ ሲፈጥሩ ከምንም፤
ቃላቸውን ወደነገር፣
ምኞታቸውን ወደገዝፍ፣
መለወጣቸው ይሆን?

ማን ያውቃል፣
እንደነበር አስቀድሞ፤
ቃል፡፡

# ምእራብ ቨርጂኒያ

የማእድን አገር፣
ሸለቆው ጋራው ድንጋይ፣ ሸለቆው ጋራው ከሰል፡፡
ቤቱ የበለዘ፣ ከተማው የተጎሳቆለ፣
የተንጠለጠለ ከጋራ ላይ፣ ካራ ቆሬን የመሰለ፡፡

ይከሳ ይሆን መሬት፣ ተርቦ?
ያገር በታች ሲሆን ደህይቶ?
ይጠወልጋል ከተማም፣ እንደሰው?
ሲቸግረው፣ ቀን ሲጥለው?

ሰው ፊቱ የገረጣ፣ ችግር የሚነበብበት፣
ከተማው የሻገተ፣ ድህነት የሰፈነበት፣
ጋራው፣ ዋሻው፣ ሆድ የባሰው፣ ሀብቱ ወርቁ ያለቀበት፤
ይሄ ነው አፐሌዢያ ምእራብ ቨርጂኒያ ማለት፡፡

እኒያን ከበርቴወች ፔንሱልቬኒያን ከብረቱ፣
ቨርጂኒያን ከከሰሉ ያላቀቁ ያራቆቱ፣
ምድሩን አገራችን፣ ሰውን ወገናችን የሚሉ፣
በሰበብ ባስባቡ አርባ ክንድ በንዲራ የሚሰቅሉ፣
ትርፍ ካለው፣ ብር ካስገኘ፣
      አገራቸውን ለማጥፋት፣ ወገናቸውን ለመሸጥ፣
                    ወደሁዋላ የማይሉ . . . . .
የኢትዮጵያን ወርቅ እንዲያወጡ፣ መለመን፣ መጋበዝ፣
              ምን እንዲልልን ይሆን ጠብ?
ለመሰለፍ ካልሆነ በቀር አብረን፣
              ያባታችን ቤት ሲዘረፍ፡፡

# ቀፎ

በሰው ቁዋንቁዋ ማሰብ፣
        በሰው ቁዋንቁዋ መማር፣
በሰው ቁዋንቁዋ መፃፍ፣
        በሰው ቁዋንቁዋ መዝፈን፣
የበታችነት ጠባይ ነው፣
        ወዶ ገባ ባርያ መሆን፡፡

ባርነት የማይጨንቃቸው፣
የበታችነት ቀንበር ማይከብዳቸው፣
የሌላውን ነገር አክብሮ፣
        የራሳቸውን ማናናቅ ሚያኮራቸው፣
ምን ያስብ ይሆን?
        ከምን ይሆን የተሰራው?
                በምን ይሆን የተሞላው?
አንጎላቸው፡፡

እዞላብድ ጀመር፣
        እኔም፣
ዘመዶቼ መሆናቸው፣
        ዘመዳቸው መሆኔም አይደል!

ባዶ ቢሆን እንጅ ቀፎ፣
        ቢኖርበትማ አንዳች ነገር፣
መች እንዲህ ይሆኑ ነበር!
        መች እንዲህ እንሆን ነበር!

# ኮሎራዶ

ሲንሸራተቱ አይተን ሀብታሞቹ በበረዶ፣
ያበሻ ልብ ሆና ነው መሰለኝ፣
        እኛም አማረን መሄድ አስፒን ኮሎራዶ።

ተያያዝነው ጋራውን ከመሸ፣
አለኛ አይታይ መኪና፣
        አለኛ ሰው የለ፤
ለካስ ኖሮታል ምክንያት እርጭታው፣
ከ ኡኘሺ ጫማ በላይ አይጠረግምና በረዶው፣
ዝግ ነበር መንገዱ ያስፒን ኮሎራዶ፣
ከተዋናይ ጋር መጋፋት ቀረ፤
ከተዋናይ ጋር መንሸራተት፣
                ወይ ነዶ!
                        ወይ ነዶ!!

በመጣንበት መንገድ አሽቆለቆልን፣
ያገራችንን ዘፈን እየዘፈን፣
ያገራችንን ዘፈን እያዘፈን።

እንቅልፍና ጨለማ፣
        በረዶ የሸፈነው ጎዳና፣
የቁልቁለት መንገድ፣
        የኮሎራዶ ተራራ፣
አብረው አይሄዱምና፣
        አይስማሙምና፣

፵፯

ትንሽ ከተማ ስናገኝ ቆምን፣
'ሚላስ 'ሚቀመስ ፍለጋ፣
መኪናችንን ማቀዝቀዣ፣
ወገባችንን ማሳረፊያ፡፡

ከመንደሩ በላይ፣ ከትልቁ ጋራ ስር፣
የሚከራይ ጎጆ አገኘን፣
ዋጋው ያልናረ ያልተንዛዛ፣
በልካችን ባቅማችን፣
ደክሞን ነበርና፣
እንቅልፍ ተጫጭኖን፣
ገላችን አልጋ ሲነካ፣
ሄድን፣ ተሰናበትን፡፡

ጥዋት ከእንቅልፌ ስነቃ፤
ጥዋት ከአልጋዬ ስነሳ፤
ድምፅ ሰማሁና ደስ የሚል፣
የሚንጨለጨል የሚንሽዋሽዋ፣
ተነስቼ ወጣሁ ከክፍሌ፣
የድምፁን መምጫ ላይ ብዬ፡፡
ኩል የመሰለ ምንጭ ነው፣
ከጋራው ላይ የሚመጣ፤
በጎጆአችን አጠገብ የሚያልፍ፣
የሌሊት ማንቀላፊያ፣
የጥዋት መንቂያ ሙዚቃ፡፡

## ፵፱

ትዝታ ሞላው ልቤን፣
የሰላሌ፣ የመተከል፣ የአጣዬ፣ የጎባ፣
ጎንበስ ብዬ ጠጣሁት፣ እንደልጅ፣
ውሀ ባይጠማኝም እንኩዋ፡፡

አ!! . . . . ....

አዋቂወቻችን ያልነኩት፣
ስልጣኔ ያላገኘው ንፁህ ውሀ፣
ሳያጣሩ ሚጠጡት፣
ሳይቀቀል ሳይፈላ፡፡

፶

# ቀለም

ምን ማለት ነው የቀይ ዳማ፣ ሰማያዊ፤
አረንጉዋዴ ደብዛዛ፣ ወይ የፈካ ሀምራዊ፤
የደመቀ፣ አይን የሚያውር ቢጫ፣
የደከመ፣ የማይታይ ግራጫ፤
ምን ነበር፣ የዚህ ሁሉ ትርጉሙ፣
አንድ ቢሆን፣ የፍጡር መልኩ ቀለሙ?

ይጠራጠራሉ ጠቢባን፣ የቀለም አብነቱ፣
መሆኑን፣ የብርሀን ሞገድ ርዝመቱ፡፡
ስለዚህ፣ ቀለም የብቸኛ ጠባይ አይደለም፣
        ፍፅምናን ያዘለ፣
በሞገድ ርዝመት የሚፈታ፣
        በብርሀን ባህሪ የቆመ፡፡

፶፩

# የጎሳ ዴሞክራሲ(ጎሳዴሞ)

ባህል፣
ተንቀሳቃሽ ነው፣
        የተረገጠ ህያውነቱ፤
በጎሳ ባላባቶች ፍላጎት፣
        የማይገታ ሂደቱ።

ባህል፣
በአምሳላቸው የሚተክሉት፣
በአምሳላቸው የሚያበድኑት፣
የሚቀርፁት የሚያበጁት፣
        አይደለም ብሀ ደንግያ፣
የህብረሰብ መንፈስ ነው፣
        ያለፈውን ማከማቻ፣
                የወደፊቱን መገንቢያ።

ተዋቸው ባላባቶቹን፣
        ለማቆም የሚታገሉ ባህልን፣
ደፍጥጥዋቸው ሲያልፍ ያውቁታል፣
        እንደማይቻል እንደማይሆን።

መብት፣
የግል ንብረት ነው፣
        የተፈጥሮ ስጦታ፣
ያለግለሰብ ፈቃድ፣
        'ማይነጠቅ 'ማይነካ።

ታዲያ እነዚህ ባላባቶች፣
የጎሳ ፈላስፋዎች፣
የሚያድሉትን ነፃነት፣
የሚቸረችሩትን መብት፣
ከየት ይሆን ያመጡት ከቶ?
ያገኙት ወድቆ ተጥሎ?

ይገርማል!!
እውነትም ጥላሁን እንዳለው፣
ለመሆን ነው አሳ ነባሪ፣
ከትንሽ ኩሬ ተገኝተው፡፡

ግን፣
መሰላቸው እንጅ አይቻልም፤
ማቆም ባህልን፣
ማደል መብትን፣
መቸርቸር ነፃነትን፣
አይቻልም፡፡

ይልቅስ የሚቻለው፣
የሆነው የሚሆነው፣
መብትን ጠቅሎ፣
ነፃነትን ቁዋጥሮ፣
ለባዳ፣
ለባንዳ፣
ማስረከብ ነው ሰብስቦ፡፡

ይሄ ነው የሚቻለው፣
የሆነው የሚሆነው፤
ይሄው ነው፡፡

፶፫

# ይገርመኛል

በህልማችሁ፣
ታውቃላችሁ ሮጣችሁ?
በህልማችሁ፣
ታውቃላችሁ በራችሁ?

በውሀ ውስጥ፣
ሞክራችሁአል ልትሮጡ?
ሞክራችሁአል ልትበሩ፣
ልትንሳፈፉ ልትመጥቁ?

መሮጥ ያስቸግራል፣
የማእከሉ እፍጋት ሲበዛ፤
መብረር መንሳፈፍ ግን ቀላል ነው፣
የተፈጥሮ ባህርይው ነውና።

እና የህልም ማእከል፣
እነዚህን ህግጋት መጠበቁ፣
ፊዚካን ሲያይ ማፈሩ፣
የአርቄሜዴስን መርሆ ማክበሩ፤

ይገርመኛል።

## መሱ (ለአምሳለ አስፋው፡፡)

«ሀ! ሁ!»  ብላ፣ ፊደል  ቆጥራ፣
ደብተርዋን ገልፃ፣ እርሳሰዋን ቀርፃ፣
ሞጭራ ሞጫጭራ፣ ፅፋ ደልዛ፣
ሳትጫወት፣ ከባቡር መንገድ ወጥታ፣
ሳትመታ፣ እንደህፃን ልጅ አጥፍታ፣
ሲያማት ሲጥላት፣ ስትተኛ ነፍስዋን ስታ፣
ከሶስት ቀን በሁዋላ ስትነቃ፣
        ምንም ነገር እንዳልሆነ፣
            መፅሀፍዋን ከወደቀበት አንስታ፣
የፈረንጁን አንብባ፤ ያበሻውን አጥንታ፣
ኪኒንዋን ሳታጉዋድል፣ በቀን ሁለቴ ውጣ፣
እንዳማይደረስ ነገር የለም፣
        ሁለተኛ ደረጃን ጨረሰች፤
            የሰው ልጅ የሰጣትን ፈተና አልፋ፡፡

ግን ለካስ ሌላ ፈተና አለ፣ ተነቦ ማይታለፍ ተፅፎ፣
ከወደቁ ማይነሱት፣ ተንገዳግዶ ተውተርትሮ፡፡

ምንም አይደል መሱ፤
ይውላል ያድራል እንጅ፣ ጊዜው ሲደርስ ወደማታ፣
ሁላችንም አለብን፣ ይህ የሚጥል በሽታ፣
ቸኮለ እንጂ ያንች፤
        የማናልፈው ፈተና ነው፤ የሁላችንም እዳ፡፡

ምናለ ቢኖር ህይወት፣ ከሞት ወዲያ፤
ለስቃይሽ መካሻ፣ ለተቀጨው እድሜሽ ማምዋያ፤
ምናለ.......

## ክፍል ሁለት

# ኢትዮጵያ

፶፯

# ይላላ ደነቦ

ቤታችን የተሰራው ከኮረብታ ላይ ነበር፡፡ ከዋናው በራፍ ብዙም ሳይርቅ ከገደሉ ወገብ ላይ ሁለት ቁዋጥኝ ድንጋዮች ነበሩ፡፡ እነዚህ ቁዋጥኞች ስር ለተቀመጠ፣ ከገደሉ ስር ትንሽ ሸለቆ ይታየዋል፡፡ ከሸለቆው አብዛኛው የኛ መሬት ነበርና እኔና ያጎቴ ልጅ ከነዚህ ቁዋጥኞች ስር ተቀምጠን ብዙ አልመንበታል፡፡ ግድቡ የት መሆን እንዳለበት፣ የሀምሌ ዝናብ እየጠረገ የሚወስደውን አፈር እንዴት እንደምናቆም፣ ትምህርት ቤቱን የትጋ እንደምንገነባ ፣ ሀኪም ቤቱ የት እንደሚሰራ፣ ምን እንደምንዘራ፣ ምርቱን የት እንደምንሸጥ፣ በስንት.........

ህልማችንን ጊዜ እንደማባከን ሳይሆን፣ ለወደፊቱ ስራችን መሰረት እንደመጣል አድርገን ነበር የምንመለከተው፡፡ በዚያም ላይ፣ ኒያላችንን ለማጨስ፣ የወላጆቻችን አይኖች የማይቃኙት ከዚህ የተሻለ ሰዋራ ስፍራ ከየት እናገኝና፡፡

አንድ ቀን እንደለመድነው ሁሉ ከነዚያ ድንጋዮች ስር ተቀምጠን ፣ በምኞት መሬቱን አርሰን፣ የምኞት ዘር ዘርተን፣ አጭደን፣ ከምረን፣ ወቅተን፣ አግብተን፣ እህሉን ሸጠን ከበርን፡፡ የህልማችን ወይም የብራችን መብዛት አደከመንና፣ እንቅልፍ እንቅልፍ አለንና፣ እንደ ተኮራረፈ ሁሉ ዝም አልን፡፡ እንኳዋንስ ዝም ተብሎለት ምንጃር ራሱ ዝምታ ነበርና፣ አየሩ ከበደ፤ ምድሩን ፀጥታ ዋጠው፡፡

እውነተኛ ፀጥታን ለማወቅ፣ እንደምንጃር ያለ ቦታ መሄድ ያስፈልግ ይሆናል። ሰማዩ «አውሮብላ» ምድሩ «መኪና» አይታይበትም። ከኛ መንደር ከውርጌቻማ፣ ፲ ኪሎሜትር ስለሚርቅ የጋሼ ዳምጤን የእህል ወፍጮ እንኳዋን መስማት አንችልም።

እንዲህ በዝምታ ተውጠን እያለ፣ ከሸለቆው ባሻገር የሚመጣ ድምፅ ተሰማን። አንገታችንን ቀና አርገን ጆሮአችንን በድምፁ አቅጣጫ ቀሰርነው። ትንፋሻችን የመስማት ችሎታችንን እንዳይቀንሰው ነው መሰለኝ፣ ላንድ አፍታም ቢሆን መተንፈስ አቆምን። የሚያየን ሰው ቢኖር፣ የደነገጡ ሚዳቆዎች ሳንመስል እንቀር ነበር?

ድምፁ እየቀረበ ሲመጣ፣ የሚዘፍኑና የሚጨፍሩ ሰወች መሆናቸውን አወቅን። እንዲያውም ሲጨፍሩ በእግራቸው የሚያደቁት አብዋራ ወደ ሰማይ ሲነሳ ይታየን ጀመር።

በመጀመሪያ ሰርገኞች መስለውን ነበር። እየቀረቡ ሲመጡ ግን፣ ሬሳ ለመቅበር የሚጉዋዙ ለቀስተኞች መሆናቸውን ተገነዘብን። ለካስ ዜማው ሙሾ ነበር፣ ይላላ ደነቦ የተባለ ሙሾ......

ይላላ ደነቦ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። ለማወቅም አልፈልግም። ለኔ፣ ይላላ ደነቦ የምንጃሬነት ምልክት፣ የምንጃሬ መንፈስ ያረፈበት አርማ እንጅ ተራ ትርጉም ያለው ሀረግ አይደለምና።

ምናልበት ስሜቴን፣ ከኔ ይልቅ የላንግስተን ሂዩዝ «ወገኖቼ» ሳይገልፅልኝ አይቀርም፡፡

*ወገኖቼ*

*ሌሊቱ እጅግ ውብ ነው፤*
*የወገኖቼም መልክ እንዲሁ፣*

*ከዋክብቱ ውብ ናቸው፤*
*የወገኖቼም አይኖች እንዲሁ፣*

*ውብ ናት፣ ፀሀይትዋም፣*
*ውብ ነው፣ መንፈሳቸው፣ የወገኖቼም እንዲሁ፡፡*

አልቃሾቹ ወደሸለቆው እንደገቡ ሁሉ ሙሾአቸውን እያወረዱ፣ የምንጃርን መሬት እየደለቁ፣ አብዋራውን እያበነኑ፣ ፀጥታውን በጩኸት፣ ዝምታውን በለቅሶ እየለወጡ፣ ሸለቆውን ጥለውት ወጡ፡፡ እኛም ወደዚያ እርጭ ወዳለ፣ የጠቆረ የጠራ የምንጃር ሰማይ ተመለስን፡፡

ይላላ ደነቦ የተባለው ግጥም፣ ያን ሌሊት ተፃፈ፡፡ ተበድለው እንደበዳይ፣ ተጨቁነው እንደጨቋዋኝ ለተቆጠሩ፣ ላባቸው ካየሩ፣ ደማቸው ካፈሩ ጋር ለተቀላቀለው ለምንጃር አራሾች ሁሉ መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡ ለጋሼ ወሮ፣ ለፀጋ፣ ለጋሼ ዳምጤ ....

፳

# ይላላ ደነቦ

ይላላ ሆይ፣ የማነው ዲሞትፎር፤
ይላላ ሆይ! ይላላ ደነቦ፤
ይላላ ሆይ፣ ታስሮ የሚፎክር፤
ይላላ ሆይ! ይላላ ደነቦ፤
ይላላ ሆይ፣ ሁሉም ነው የሚያውቀው፣
ይላላ ሆይ! ይላላ ደነቦ፤
ይላላ ሆይ፣ የዚያ የጀግና ነው፤
ይላላ ሆይ! ይላላ ደነቦ።

እንዲያ ነው የምንጃር ገበሬ ሲያለቅስ፣
የወዳጁን ሬሳ ሲሸኝ፣
ወገኑን ወደአፈር ሲመልስ፤
በገበሬ እግሩ ሲጨፍር፤
እረም እረም ሲል መሬቱ፣
ከርቀት ለሚያዩ፣
ከርቀት ለሚመለከቱ፤
ይመስላቸው ይሆናል፣
ደስ ብሎት የሚዘፍን፣
ይሄ ገበሬ ህዝብ ሲከፋው፣
ይሄ ገበሬ ህዝብ ሲያዝን።

፳፩

# እውነት አትለካም

ያዩትን ያመኑ፣
ወግ አጥባቂ ናቸው፣
ለውጥ የሚያስፈራቸው፡፡

አስተዋይ ያልሆኑ፣
ያባታቸው ልጆች፣
ባህል አክባሪዎች፤
ናቸው ያልተካዱ፣
ያዩትን ያመኑ፡፡

አሄሄ!!

ማየት መች ሆነና የእውነት መለኪያው፣
መስማትስ መች ሆነ የእውነት መለኪያው፣
ወይ እውነት የለችም፣
ወይም አትለካም፡፡

፳፱

# ጠብታ

ምን እንደገፋቸው ሳይታወቅ፣
ከወዴት እንደተነሱ፣
የሰው ልጆች እንደውሀ፣
ጠ-ብ ይላሉ፤

በብርሀን ውስጥ እንደሚያልፍ፣
መኖሩን እንደሚለፍፍ፣
ጠብታ፣

እያንፀባረቁ፣
ብልጭቹጬፍኤፍስኤኤሽፍዙጥፕዙድንዙ
ዴልጭቹጬፍኤፍስኤኤሽፍዙጥፕዙድንዙ ዴልጭ እያሉ፤
እየቦረቁ፣
እየጨፈሩ፣
እየዘለሉ፣
የብርሀኑን ወሰን ያልፋሉ፣
ይጠፋሉ።

አይታወቅ የት እንደሚያርፉ፣
የት እንደሚደርሱ፤
ከየት እንደመጡ፣
ወዴት እንደሚጉዋዙ።

ምናለ ሁሌ ቢያንፀባርቁ፣
ጠ-ብ ባይሉ፣
ባይሆኑ የውሀ ሽታ፣
ጠብታ።

# መደነቅ ይሉኝታ ነው

ሰው ይገርማል፣
ህይወቱን ይለውጣል፣
ለመከበር፣
ለመደነቅ፡፡
አይመረምርም ክቡርነትን፣
ታላቅ መሆንን፣
መደነቅን፡፡

ያሳዝናል የሰው ልጅ፣
ለይሉኝታ ሲገዛ፣
ለይሉኝታ ሲሸበር፤
ይሉኝታ ነው መደነቅ፤
ይሉኝታ ነው መከበር፡፡

# ምን ቸገረህ!

ሂትለር!
አሁን ሰው ሁሉ ይጠላሃል፤
ደግ አላደረግህም ይልሃል፤
ያወግዝሃል።
ዳሩ አንተ ምን ቸገረህ፣
የምትፈልገውን አድርገሃል፤
ከምኞትህ ወሰን ባትደርስም፣
የውበት ስሜትክን አርክተሃል።

መሞትህን አውቆ፣
አለመኖርህን ተረድቶ፣
የሚፈራህ ባይፈራህ፣
የሚያከብርህ ባያከብርህ፣
የሚወድህ እንኳዋን ቢጠላህ፣
ምን ቸገረህ!

# ልወቀው

ሀያል አምላክ ካለህ፣
አለምን በቃልህ የሰራህ፣
ምንም የማይሰወርህ፣
አጠፋሁ?
          ተሳሳትኩ?
                    ምን በደልኩ?

የፍጥረት መጀመሪያ ፣
          እውነት ካለህ የህጎች ሁሉ መሰረት፣
ንገረኝ ልወቀው፣
          ምን ማለት እንደሁ ማጥፋት፣
          ምን ማለት እንደሁ ማልማት፡፡

ይኖር ይሆን ማጥፋት፣
               ማበላሸት፣
ይኖር ይሆን ማልማት፣
እውነትን በውነት ላይ መገንባት፣
ሀያሎች እንዳላችሁ፣
          አለምን የምታዙ ፣
                    የምትገዙ፣
ንገሩኝ ሚስጥሩን፣
          ልወቀው፡፡

፳፮

# እስቲ አስቡት

ያን ወጣት ልጅ ሆናችሁ፣
እስቲ አስቡት፣
          ያበደ ውሻ ነክስዋችሁ።

የምትወድዋት እናታችሁ፣
          አይታችሁ፤
ከሩቅ ሆና፣
መለከፋችሁን ተመልክታ፣
ፍቅርዋን ለመግለፅ፣
          አልቅሳ፤
          አንብታ፤
እንዳትጠጋችሁ ግን፣
          በሽታውን ፈርታ፤

የምትወድዋት ልጅ ፍቅረኛችሁ፣
ሞት እንኳዋን አይለየንም፣
          የምትላችሁ፣
ከሩቅ ሆና፣
          ተመልክታ፣
እንደናታችሁ ሁሉ፣
          መጠጋቱን ፈርታ፤
የሩቅ ፍቅርዋን ለመግለፅ፣
እስዋም አልቅሳ፣
          አንብታ፤
እስቲ አስቡት።

የሚያዝንላችሁ አጥታችሁ፣
ጭንቀታችሁን የሚካፈል ጠፍቶ፣
ብቻችሁን ቀርታችሁ፡፡
ሞት እየቀረበ ሲመጣ፣
የምታደርጉት ሲታጣ፣
ስለ ሉዊስ ፓስተር ሰምታችሁ፣
የመዳን ተስፋ ኖርዋችሁ ሳይሆን፣
እንዲያው፣
ለምናልባቱ ብላችሁ፣
«ይጠጋኝ ይሆን?
ያባርረኝ ይሆን ከቤቱ?»
እንዲያ ሆኖ ጭንቀታችሁ፣
እስቲ አስቡት፣
ሉዊስ ፓስተር ዘንድ ሄዳችሁ፡፡

እንደናታችሁ ሳይሆን፣
ወይ እንደፍቅረኛችሁ፣
ትከሻችሁን መታ-መታ አርጎ፣
አይዝዋችሁ ቢላችሁ፣
ትድናላችሁ፤
ታምኑት ነበር ቃሉን?
ወይስ ትሉ ነበር፣
«የሀኪም ልማዱ ነው፣
የበሽተኛ ትከሻ ይዞ አይዞህ ማለት፣
በርሱ ፈቃድ ይመስል፣
ሰው የሚድን፣
ሰው የሚሞት፡፡»

መድሀኒት ብጤ ቀምሞ፣
          ያ ትልቅ ሰው ከትብዋችሁ፣
ይቀልዳል፣ ብላችሁ፣
የሚጫወት መስልዋችሁ፣
የጣር ሳቅ ስትስቁ፣
          እስቲ አስቡት፣
በውሻ በሽታ ተለክፎ፣
          ሰው አልዳነ ከዚያ በፊት።

እንደነፍሰ ጡር ሴት ፣
          ቀን ስትቆጥሩ፣
          ሀያ፣ ሰላሳ ቀን፣ ሞላችሁ፤
ሰላሳ አምስት፣
ሰላሳ ስምንት፣
ሰላሳ ዘጠኝ ቀን ሆናችሁ፣
ያ በሽተኛ ውሻ ከነካችሁ።

አርባ ቀን ሞላ፣
          ምንም የለ፤
           አይፈልጣችሁ፣
           አይቆርጣችሁ፤
ኧረ ደህና ናችሁ።

ዳናችሁ፤
ታምር ነው ተባለ፤
          ከሞት መትረፋችሁ፤
መጣች እየሮጠች፣
          እናታችሁ፤
እጆችዋን ዘርግታ፣
          ልታቅፋችሁ፣

ልትስማችሁ፤
መጣች ፍቅረኛችሁ፣
እየሳቀች፣
እየተንደረደረች፣
አዲስ ተረት ልትጀምር፣
ስትሞት እሞታለሁ ልትል፡፡

ምን ይታያችሁ ይሆን፣ ይሄኔ፣
እስቲ አስቡት፡፡

# ከሰውነት ወደ እቃ

ቀኃሥ ሆስፒታል ቆሜ፣ አንድ ቀን፣
ለመታከም ስጠብቅ፣ ወረፋየን፣
ታማ፣
መራመድ ተስንዋት፣ ደክማ፤
አንድ የምታሳዝን ሴት መጣች፣
በሚሽከረከር አልጋ እየተገፋች።

ነበርና ያለፈችው ባጠገቤ፣
አየሁዋት፣ ሲንከባለሉ አይንኖችዋ፣
          አየችኝ ሲንከባለል ልቤ።
አይቻታለሁ አለች፣
ይነቃነቃሉ ጣቶችዋ መች ሞተች።

አንድ ወንድ፣ አንድ ሴት፤
          በግራና በቀኝዋ ቆመው፣ ያይዋታል፤
አንዳንዴም ፈገግ ይሉላታል፤
ሴትየዋ፣ በሁለት እጃቸው፣ እያረጉ ጭብጥ እጆችዋን፣
እያዩ፣ አንዴ ሰውየውን፣ አንዴ እስዋን፣
ይላሉ «ተሽልዋታል፣
ኧረ ትኩሳቱ በርዶላታል፣
ተሽልዋታል።»

መንከባለሉን አቆመ ድንገት አይንዋ፣
በክፍሉ ጣሪያ ላይ ተሰካ ካንድ ቦታ፤
ምን አይታ ይሆን የሚያምር፣
እንዲያ የሚያፈዝ ውብ ነገር?

፸፩

አየሁዋቸው አይኖችዋን ፣
ፈዘው ቀሩ፣
        ቀሩ፤ ምን ሆነው ይሆን?

መጣ ሀኪሙ፣
አዳመጠ፣ የልብዋን ትርታ በልቡ፤
አዳመጠ፣
አዳመጠ፣
አይኮማተር ግንባሩ፣ አይከፋ፣
ወይ ደስ አይለው፣ ፊቱ አይፈካ፤

ሴትየዋ ፈገግ እያሉ፣
የሀኪሙን ፊት እያዩ፣
«ደህና ናት፤ አይደለችም?
ትድናለች፤ አትድንም?»
                ይሉታል፤
ፍቅራቸው ፍቅሩ፣
        ቁዋንቁዋቸው ቁዋንቁዋው ይመስል፤

ሲያዳምጥ ዋለና፣ ቀና ብሎ ፈረንጁ፣
ሞታለች አላቸው በምልክት በጁ፣
ውሰዱ አለ፣ ሬሳችሁን፣
ውሰዱ አለ፣ እቃችሁን።

ያሳዝናል፤
    በደቂቃ፣
ከሰውነት ወደ እቃ።

# አማራ

የገዥርው መደብ ይባላል፣
የሚበላው አጥቶ እየተራበ፤
ልብ ያለው አማራ ልብ ያርገው፣
የወደፊቱን ያነበበ፡፡

ያለደም ስርየት የለም ተብሎ፣
የሌሎች ሁሉ ግፍ ተደምሮ፣
መዳብ የሌለው መሬቱን፣
ቤንዚን የሌለው መሬቱን፣
የሚቆፍረውን አማራ
ከገደል ጫፍ ተንጠልጥሎ፣
ሊያደርጉት መሆኑን ጭዳ፣
ተወልዶ ባደገበት ባዳ፣
ልብ ያለው አማራ ልብ ያርገው፣
አርቆ የተመለከተ፣
የወደፊቱን ያነበበ፣
ሂደቱን የገመተ፡፡

ስንት በደል ተፈፀመ፣
ኧረ ስንት ግፍ ተሰራ፣
በስምህ፣
አማራ፡፡

፹፫

# እውነት መሰል ውበት

መች ይሆን ስክዋር፣
የሚመር፤
መች ይሆን እሬት፣
የሚጣፍጥ፤
ከማር ወለላ የሚመረጥ፡፡

አይመስለኝም ይህ ቀን የሚደርስ፣
የጣእም ስሜታችን የሚለወጥ፤
መምረር ምን እንደሁ ባናውቅም፣
መጣፈጥ፡፡

# መፅሀፍ ቅዱስ

አሁንስ ልቤን ይነካው ጀመር፣
          መፅሀፍ ቅዱስ፤
ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፣
          የሚለውን ሳስታውስ፡፡
በማሰብም ጭምር ነው፣
          ያሰበውን በማስተማር መብቱ፣
የተማረውን በመምረጥ ነፃነቱ፡፡

# ሌብነት ሲደነቅ

«የሰማይ አእዋፍን ተመልከቱ፣
አይዘሩ፣
          አያጭዱ፤
                    በጎተራም አይከቱ፡፡»

ታዲያ ምኑ ነው ቁም ነገሩ?
          ምኑ ነው እፁብ ድንቁ?
የተዘራውን መዝረፉ?
          የተሰጣውን መስረቁ?

ታምረ መለኮቱ፤
          ከሆነ ሌብነቱ፣
ሰውም እኮ አያቅተው፣
          መንጠቁ፤
                    መቀማቱ፡፡

ችግሩ ይበዛል ብሎ ነው፣
                    ህግ ከጠፋ፣
ደካማው ይጎዳል ብሎ ነው፣
          የጉልበት ኑሮ ከተስፋፋ፡፡

ኧረ ክፋም አይደል፣
          የሰው ልጅ መጠበቡ፣
የሌላውን ሳይነካ፣
          ለራሱ ኑሮ ማሰቡ፡፡

፷፯

## ፍላጎቴ

ፈልጌ አልተወለድኩም፣
　　　　ፈልጌም አልሞትም እኔ፤
መኖሬ ነው ፍላጎቴ፣
　　　　ይህን አለም መውደዴ።

## ጉራ (ለቹ ጉቬራ)

ተፈጥሮ፣
          በማያውቀው ምክንያት፣
መፈለጉን ወይም አለመፈለጉን ሳይጠየቅ፣
የማያውቀውን ኑሮ እንዲኖር ተፈርዶበት፣
ለምን እንደሁ ሳይገባው፣
          ሞትን ጠልቶ፣
ምቾት መቀማጠልን ወዶ፣
          ስቃይን ሸሽቶ፣
የሚወደውን ወስኖ፣
          የሚጠላውን ወስኖ፣
የሚወደው ነገር ጥሞት፣
          የሚጠላው ደግሞ አንገሽግሾት፣
ከተደላደለ ወዲያ የህይወት ፍች ተረስቶ፣
መስዋእት ሁን ይሉታል፣
    የሌላውን እንዲያመቻች የራሱን ኑሮ አበላሽቶ።

አለምን፣
ከልደት በፊት አልኖረበት፤
ከሞት በሁዋላም አይቆይበት።

ታዲያ ይህችን ምድር፣
          የደስታ ዘመኑን፣
በልማድ የወደዳትን፣
          በልማድ ያፈቀራትን፣
እንዴት ትትዋት ይሙት?
           እንዴትስ አቁዋርጦ ይዘን?

ያ መስዋእት የሚኮንለት ፍጡር፣
የራሱን ኑሮ ሊያመቻች አይደል፣
የራሱን ኑሮ ሊያሳምር?

«ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፤»
እያሉ ሲያታልሉ፣
ያዳም ልጅ ልክ ነው ይላል፣
ፍችው እንደገባው ሁሉ፡፡

ምንድን ነው መስዋእትነት?
የራስን ኑሮ አበላሽቶ የሌላውን ማቃናት፡፡
አጉል ባህል ነው እንበለው፣
የአለምን ህዝብ ያሞኘ፣
መስዋእትነት እንደሁ ጉራ ነው፣
በውሸት ባህር ውስጥ የዋኘ፡፡

፸፱

## ምን ያደርግላቸዋል?

አምላክን ካላየን ይላሉ፣
　　　　የራሳቸውን አይተዋል፤
　　　　　　　　የሰው ምን ያደርግላቸዋል?

፲

# ንክች

«እችክ እችክ፣
እትት ትት እትትት፣
ቤት የለ፣
        የት ልግባ፣
        የት ልጠለል፡፡
ዛፍ!
        በስማብ!
                ዛፍ!
በእለተ ቀኑ አርሼ፣ ቅዱስ ገብሬል፣
        መች ይተወኛል፣
        መች ይምረኛል፡፡

ዛፉንስ አልጠጋም፣
        ይውረድብኝ እንጅ ዶፍ፣
የደፈረውን ለመቅጣት፣
        ገብሬል ምን ጊዜም ቢሆን አይሰንፍ፣
ምኔም አይተርፍ፣
ዛሬ፣ ምኔም አይተርፍ፡፡»

ቤቱ ገባ፣
        የገብርኤል ብራቅ ሳይመታው፣
የዛሬን ተወው፣
        የዛሬን ማረው፡፡

ሁለተኛ ስራ ንክች!
በገብሬል ምድር?
        ንክች!

፺፩

# ስልጣኔ ያልሻረው ችግር

ተፈጥሮ ውበት ነው፤
እውነትነት የሌለው።

ወይም፣
ተፈጥሮን እውነት ካልነው፣
ውበት የለም፣
በዚህ አለም።

ግን ማታለል ይሆናል፣
እራሳችንን፣
ውበት ማለቱ፣
እውነት ማለት ስለሚሆን።

ከዚያም ይከተላል፣
ችግሩ፣ የዘመኑ፣
አምባ ገነን መሀይሙ፣
አምባ ገነን ምሁሩ።

አዳሜ የውበት ስሜቱን ያረካና፣
የሌላውን ይጠላና፣
የሌላውን ይነቅፍና፤
«እኔን ብ-ቻ ተቀበሉ፤
ለእኔ ብ-ቻ አሜን በሉ፤»
ይላል፤
«የሌላው ውበት፣
የኔ ግን ነውና እውነት።»

፹፪

# የእውቀት መለኪያ

ሰውየው የቻይኖችን ብልህነት ሰምቶ፣
የእንግሊዘኛ ቋንቋዋ አለመቻላቸውን ተረድቶ፤
እንዲህ አለ፡፡

«እነዚህ ቻይኖች ይላሉ እውቀት አላቸው፣
ሲደነቅ ሰማሁ ትምህርታቸው፣
ሲባል ሰማሁ ጠቢብ ናቸው፣
የእንግሊዝ አፍ ካላወቁ እምኑ ላይ ነው ጥበባቸው?
የፈረንሳይ ካላወቁ ኧረ እንዴት ነው ትምርታቸው?»

እንዲያ ነው አባቶቻችን የሰው እውቀት ሲለኩ፣
የተማረውን ሲያደንቁ፣
        ያልተማረውን ሲንቁ፡፡

# በተስፋ ቢደሰቱ

የሰውን የውበት ድንጋጌ ያላሟሉ፣
ደረጃውን ያልጠበቁ፤
ህበረሰቡ የጠላቸው፣ የሸሻቸው፣
እነሱም የተገለሉ፣ የራቁ፤
የተፈጠሩ ለስቃይ፣
ዘወትር የተጨነቁ።

አቦ ምናለ ቢያልሙ፣
ለሌለ ነገር ቢሰግዱ፤
የሌለ ነገር ቢያመልኩ።

ምናለ ገነትን ቢመኙ፣
በሀሳብ ቢመለከቱ፣
ህይወት መራራ ብትሆንም፣
በተስፋ ቢደሰቱ።

«አምላክ የለም» ባትልዋቸው፣
የቀረቻቸውን አንድ ተስፋ
ባትነፍግዋቸው፣
ባትነጥቁዋቸው፤

ምናለ።

# እርሻ

የሚጨበጠውንም ሆነ የማይጨበጠውን ሲያስስ፣
ሀሳቤ አለምን ሲዳስስ፤
ያለሁበትን ስረሳ፣
ምኞቴን በአይነ ህሊና ስመለከት፤
በሚያምር እርሻ መሀል፣
ጉብ ካለ ስፍራ፣
ታየችኝ አንድ ቤት፤
የኔ ቤት፡፡

ታየኝ፣
ጊዜው ክረምት ሆኖ፣
አገሩ ደመና ለብሶ፣
መሬቱ በጭጋግ ታፍኖ፡፡

ወደውጭ መውጣት ቀሮኝ፣
የቤት ልብሴን ለብሼ፣
በሚወዛወዝ ወንበር ላይ፣
በእንግዳ ቤት ተቀምጬ
እሳት በሰፊው ነዶልኝ፣
መፅሀፍ ብጤ በጄ ይገኘ፣
ራሴን አየሁ በሀሳብ፣
በምኞት እንቅልፍ ፈዝዤ፡፡

ዥ- ው፣
ዥ- ው፣
ዥ- ው፣
ይላል የተቀመጥኩበት ወንበር፣

ምንም ድምፅ አይሰማም፣
ወንበሩና ወለሉ፤
ሲጋጠሙ፣
ሲላቀቁ፣
ከሚያሰሙት በስተቀር።

ማንበቤን አቆምኩና ተነስቼ፣
እንደደከመ ሁሉ፤
አንድ ሁለቴ አዛግቼ፤
መኝታ እንዳልተስማማው፣
መቀመጫ እንደቆረቆረው፣
ወገቤን በጄ ይዤ፣
ኧረግ! ኧረግ! ብዬ፣
እጆቼን ዘርግቼ፣
ተንጠራርቼ፤
ከፈትኩት፣ የመስተዋቱን መጋረጃ፣
ሰፋ አርጌ፤
ሜዳውን ልመለከት ፤
ግቢዬን ልቃኝ ባይኔ።
ግን ጭጋጉ አፍኖ፣
ማየት አልቻልኩም አርቄ፤
ያሉበትን ሜዳ እነቡሬ፣
ያሉበትን ሜዳ እነቡኖ።

ትንፋሼን ስተነፍስ፣
ከመስኮቱ ሆኜ፤
እንፋሎቱ ተጋገረ፣
ቀዝቃዛ ነገር አገኘ።
እንደ ህፃን ልጅ ተጫወትኩ፣
ስሜን በጣቴ እየፃፍኩ።

ሁዋላም ገርሞኝ ለራሴ፣
ጨዋታዬ፣
መስተዋቱን ስጠራርግ፣
የፃፍኩትን ሳነሳ፤
ሜዳው ተገልጦ አየሁት፣
ያፈነው ጭጋግ ሳሳ።

ከለምለሙ ሜዳ ውስጥ፣
ከነጩ አጥር ባሻገር፣
የሚያሳዝኑ ውብ ላሞች፣
ጥቁርና ነጭ ዥንጉርጉር፣
ተነርቶ ጡታቸው፣
ፈርከክ-ፈርከክ ሲሉ መራመድ አቅትዋቸው፣
በሀሳብ ቤቴ ተቀምጬ
አየሁዋቸው፤
አለምኩዋቸው።

ምን ያል የደስታ ኑሮ ነው፣
እጅ መንሳት የሌለበት፣
ሰው የራሱ ጌታ የሆነበት፣
ሰው የራሱ ሎሌ የሆነበት።

# ውበት

(በጅምር ከቀረ ድራማ የተወሰዱ ግጥሞች)

\- ፩ -

ሰው ተፈጥሮን ካዘዘ፣
ያምላክን ባህሪ ከወረሰ፣
ሰው አምላክ ነው፤
አምላክም ሰው።

እግዜር ምቀኛ አይደለም፣
ሌላ ሲያውቅ የሚቀና፣
የሰው ሁሉ በላይ በመሆኑ፣
የሰው ጠባይ ትትዋልና፤

ቅናትና ምቀኝነት ምንጫቸው፣
ውበት ነው አካላቸው፤
ውበት ነው ፍጥረታቸው፣
መሰረተ ኑረታቸው።

ተፈጥሮን የገዛ አምላክ፣
ተፈጥሮን የፈጠረ ፈጣሪ፣
እንዴት የውበት ስሜት ይኖረዋል?
አለዚያ ነገሩ ተገላብጥዋል፣
ተፈጥሮ እርሱን ይገዛዋል።

፹፰

ተፈጥሮ የገዛው እንዲህ፣
የጎደለው ፍፅምና፣
ሊሆን አይችልም አምላክ፣
መለስተኛ እግዜር የለምና፤
ይሆናልና ፍጡር ደካማ፣
እንደሰው ሁሉ፤ እንደኛ፡፡

- ፱ -

አለም እኩል አይደለችም፣
እኩል ብትሆን አትጣፍጥም፤
እኩል ብትሆን አትጥምም፡፡

እኩልነት ፣ ትክክለኛ ፍርድ፣
አይታየኝም ትርጉማቸው፤
ሀሳቦች የሚገቡኝ፣
ድርጊቶች፣ የሚስማሙኝ፣
ነው፤ ተቃራኒ ሲኖራቸው፡፡

ትክክከኛ ፍርድ ምን ማለት ነው?
የተዛባው ከሌለ፤
መደሰት ማለት አይገባኝም፤
የተቸገረ ሰው ካልኖረ፡፡

አረመኔ ነኝ ማለቴ አይደለም፣
የሰው ስቃይ ደስ ይለኛል፤
ብቻ ችግር ካልተደነገገ፣
ደስታም ትርጉሙ ይጠፋብኛል፡፡

- ፫ -

ያወራሁት ስለ እምነት ነው፤
        በተስፋ ስለሚጠበቅ አለም፤
አምጣ ከተባልኩ ማስረጃ፣
ካቀረብኩማ ማረጋገጫ፣
እምነት መሆኑ ቀርቶ፣
        እውቀት መሆኑ አይደለም?

እምነት አለማወቅ ነው፣ ድንቁርና፤
እውቀትም ከዚህ አይሻል፣
        የማይጨበጥ ህልም ነውና፤
                ፍፅምና፡፡
ስለዚህ፣

ወደድንም ሆነ ጠላን፣
እምነት ነው ባህርያችን፣
የኢምንትነታችን አርማ፣
                ውበታችን፡፡

- ፬ -

ሁሉም ጨካኝ ነህ ይለኛል፣ የሰው ስቃይ ማይሰማህ፣
የማታስብ የማትራራ፣ ልታዝንላቸው ለሚገባህ፣
ጨካኞችስ እነሱ ናቸው፣ የኔ ስቃይ ያልገባቸው፣
እኔ ምን ላርግ?

፺

ብዙ ጠባይ አለኝ፣ ህብረ ሰቡ ያስተማረኝ፣
ህብረ ሰቡ ያስለመደኝ፡፡

ሽለላ ስሰማ መቅበጥበጤ፣
ካሳ ክራሩን ይዞ፣ ፋኖ ፋኖ ሲል መደሰቴ፣
ህብረ ሰባዊ ተፅእኖ ነው፤ ምክንያተ አልቦ፣
አንዴ ከተያዝን ከተለከፍን የማንላቀቀው ተስቦ፤

ታዲያ ይህን የማይለቅ በሽታ፣
እንደጤንነት ቆጥሬው አብሬ በመኖር ፋንታ፣
አልያዘኝም ብየ ብለፍፍ፣ ለቆኛል ብየ ባወራ፣
የውሸት ኑሮ መኖሬን ስለማውቅ፣
ከበሽታዬ ጋር የማይመሳሰል፣
አለም ህልም ነው ምትሆንብኝ፣
ትንሽ ነገር ድቡልቡል፣
ስትዋሽ የምትሽከረከር፣
ስትዋሽ የምትንከባለል፡፡

- ኛ -

ጥፋተኛ አንች አይደለሽ፣
ጥፋተኛውስ እኔ፤
የንዋይ ሰው መውደዴ፣
የንዋይ ሰው ማፍቀሬ፤
በገንዘብ የገዛሁዋትን፣
በገንዘብ አትገዛም ብየ ማመኔ፤

ጥፋተኛውስ እኔ፡፡

- ፯ -

የሰው ፍርድ ስሜታዊ ነው፣
        ስሜት ያልነካው ፍርድ አናውቅም፣
እንዲያም ቢባል ግን፣ ማየት
        የእውነት መለኪያ አይደለም፤
ውሳኔ እውነት ሚሆነው፤
የውሸት ጎዳናው ሲዘጋ፣
        ይቻልታው ሲምዋጠጥ ብቻ ነው፡፡

ምንም አርጉ ብየ አልጠይቅም፣
        ተንተርሳችሁ ይህንን ህግ፣
እንደማትችሉ ስለማውቅ፣
እንደማንችል ስለማውቅ፣
አልጠይቅም፡፡

ኪን

# እቃ

የተረሳ እቃ አትሁኑ፣
　　　　　　የወደቀ፤
ልምላሜውን ያጣ ተክል፣
　　　　　　አበባው የደረቀ፣
　　　　　　የጠወለገ፤

የተረሳ እቃ አትሁኑ፣
　　　　　　የወደቀ።

፺፫

# ህልም ቢሆን

ያስደንቃል ማየቱ፣
ሲራወጥ ለገንዘብ ፍጥረቱ፤
ለክፋት ሲቸኩል፣
አልነጋም ሲለው ሌሊቱ፤

የራሱን ሲያመቻች፣
የራሱን ሲያሳምር፣
ወገኑን ከትንኝ ሳይቆጥር፣

አይሞት ይመስል ሲንገበገብ፣
እውነት ህልም ቢሆን ማይታሰብ፣
እንዲያው መና ቢቀር ልፋቱ፣
ህልም ሆኖ ቢሆን እውነቱ፣
እንዴት ባሳቀኝ በገረመኝ፣
የሰው ዘር ለምንም መዋተቱ።

፺፬

# ህይወት ሰው አትንቅም

ህይወት ትረሳለች፣
ንቃ ትተዋለች፡፡

አይቶ ስትንቀው፣
        ስትረሳው፣
         ስትተወው፣
ሰው፣
እሱም ይረሳታል፣
ጨርሶ ይተዋታል፡፡

ሲጠየቅ ሰበቡ፣
ኬት እንደጀመረ፣
        ንቀቱ፣
          መርሳቱ፣
«እኔ ነኝ!» ይለናል፣
        «የናቅሁዋት፣
          የተውኩዋት፣
ህይወት ሰው አትንቅም፣
        ሰው ነው የሚንቃት፡፡ »

# ውሽታሞች

የተገለበጠ መኪና፣
ከሩቅ ሆነው ያዩና፣
«በስመአብ!» ይሉና፣
ያማትቡና፤
መኪናቸውን አቁመው፣
አንገታቸውን ብቅ አርገው፣
«ሰው ተረፈ?» ይላሉ፤
ከገንዘብ ሰው እንደሚመርጡ፣
ከገንዘብ ሰው እንደሚወዱ።

ውሽታሞች!!

# ዝናብ

ጫት ቅመን፣
ለፀሎት እንደተቀመጠ ሁሉ፣
        ፀጥ አልን፡፡
ሀይለኛ ድምፅ የሚሰማው፣
ጫቱ ሲቀነጠብ፣
        ጉንፋናሙ ሲስል ነው፡፡

ተመካክረን የጀመርነው፣
ተማምለን ያደረግነው፣
የሚመስለው ፀጥታ፣
የማይፈርስ፣
        የማይሰበር፣
                የሚመስለው ዝምታ፣
ፈረሳ!
ተሰበራ!
እንደሰው ልጅ ሀሳብ ሁሉ፣
        እንደሰው ልጅ ስራ፡፡

ሻይ ቀረበ፣
        ሚርቃና ተባለ፣
ወሬው ሞቀ፣
        ጨዋታው ጋለ፣
ዝምታ የሚሉት ፈሊጥ እንዳልነበር፣
ዝምታ የሚሉት ፈሊጥ እንደሌለ፡፡

## ፺፯

ወሬያችንን ስንኮመኩም፣
          ስንቀዳ፣
ከጨዋታ ገንዳ፣
በረዶ ቀላቅሎ አይመጣም!
          ዝናቡ፣
አቶ እንደልቡ፣
አውሪው አፉን ያነቃንቃል፣
ሰሚውም ጆሮውን ያስጠጋል፣
አይ ዝናብ፣
የፍጥረትን ምኞት፣
          የሰውን ፍላጎት፣
                    መች ያውቃል።

## ዋይታ (ለጀነራል ሞገስ በየነ)

አንች ወንበር፣
እንደድሮው መሰለሽ፣
ያ ጌታሽ፣
ተመልሶ መጥቶ፣
ተኝቶብሽ ተንጋሎ፣
ያካባቢሽን አየር የሚያሸት፣
ባንችም ሆነ በቦታው የሚደሰት፡፡

አይምሰልሽ ሞኝቱ፣
አይመለስም ጌታሽ፣
 እንደወጣ ቀርትዋል ከቤቱ፡፡

«ከእንግዴህ አያረጅ ሰውነቴ፣
አይጣመም ብረቴ፣
ሽራዬም አይጎደጉድ፣
 አይቀደድ፣
እፎ-ይ ተገላገልኩ፡፡»

«ምስር ብላ፤» እንዳትይኝ፣
«የምስራች ስለነገርከኝ፤»
ያንች እፎይታ፣
ለኔ ነውና ዋይታ፡፡

፺፱

# እውነተኛ ስቃይ

የፈለጉትን አለመሆን፣
          የፈለጉትን አለማግኘት፣
አይደለም መቸገር፣
          አይደለም መሰቃየት፡፡

የማይፈልጉትን መሆን ነው፤
          ስቃዩ፣
             ጭንቀቱ፤
ያልፈለጉትን መስራቱ፡፡

ካ

# ውሸት

ውሸት ልንገራችሁ፤
        ሰው መሬትን ለቀቀ፤
        ህዋን ሰነጠቀ፤
        ጨረቃን ረገጠ፤
አልክዋችሁ፤
ምን ትሉ ይሆን?
        እስቲ ልስማችሁ፡፡
ይሄማ ተረጋግጦ፣
        ምነው ሰው መሬትን ለቆ፣
        ህዋንም ሰንጥቆ፣
        ጨረቃን ረግጦ፣
ትሉ ይሆናል፤
        አይ ሞኝነት!
እውነትን ከውሸት መለየት አቅትዋችሁ፡፡

ሰው ማለት ምንድን ነው?
ውሸቱ እዚህ ላይ ነው፡፡
        እኔም፣ አንተም፣
        አርምስትሮንግም፣ አይነስታይንም፣
        ነጮችም፣ ጥቁሮችም፣
ሁሉም ሰው?
ተው!
ኧረ ራስክን አታታል ተው!
ሁሉም አይደለም ሰው፡፡

ሰው ሁሉ በተፍጥሮው እኩል ነው፤
የሚሉት ፍልስፍና ሰምቼ፣
ነበር ተቀብዬ፣
እውነት ነው ብዬ፡፡
ማየት ደጉ፣
መኖር ደጉ፣
ተገለፀልኝ፣ የስሚዝ አስተሳሰብ የድንቁ፣
የቬርወርድ ፍልስፍና የፃዲቁ፡፡
ለካስ ሰው ሁሉ ሰው አይደለም፣
ሲመስለኝ የነበረም አልነበረም፡፡

መዝገበ ቃላት ተሳስቶ፣
አልተሳሳትኩም ቢል ተነስቶ፣
ምነው ተሳስተህ፣
ሰው ያልሆነውን ሰው ብለህ፣
ብለው ይከራከራሉ ጠበቆቹ፣
እስሚዝ ቬርወርድና ነጮቹ፡፡

እስሚዝም ትክክል ነው፤
ቬርወርድም እውነት ነበረው፤
የነጭ ትርጉሙ እንደሁ ሰው፤
ሌላውማ.......!
ሌላውማ፣ ከድንጋይ ዘመን ጀምሮ ድንጋይ ነው፡፡

የንዴት ነው አትበሉኝ፤
አትችሉምና የድንጋይ ንዴተኛ ልታሳዩኝ፤
ቀልድ ነው በሉ የድንጋይ ጨዋታ፣
ይመርብን እንጅ በስማችን፣
ይሄ ነው እንግዴህ የኛ ፋንታ፡፡

፻፪

# ጊዜ ሲቆም

ምንጩን ዘለለና ተሻገረ፤
እርስዋ ግን ፈራች፣
 ሳትሻገር ቀረ።
እጅዋን ዘረጋችው፣
 ተንጠራርታ፤
እርሱም ዘረጋላት፣
 ተንጠራርቶ፣
ዘለለች፣
 አሻገራት ጎትቶ።

ተወርውረው እንደመጡ፣
 ጡቶችዋ አረፉ ከደረቱ፣
እጆችዋም ካንገቱ።
 ፈዘዙ፣
 ደነዘዙ፣
ያለፈ ነገር ተረሳቸው፣
መጭውን ማሰብ ተሳናቸው።

እለተ ምፅአት ደርሶ፣
ክርስቶስ ቃሉን አክብሮ፣
 ወደዚች ምድር ተመልሶ፣

«ቁሚ አትሽከርከሪ አንች አለም፣
በቃሽ መልፋት፣
 በቃሽ መድከም፣
ተወው ንቅናቄህን፣
 እርጋ በያለህበት፣

ጊዜም ቁም አትሂድ፤
ይበቃሀልና የሄድከው፣
ይበቃሀልና ያለፍክበት፣
እንግዲህ አንተም ይለፍብህ፣
መታለፍንም ተመልከት፡፡»

እንዲያ ያለ ነው የመሰላቸው፣
ነገሩ የሆነባቸው፡፡

# የዘመኑ ህብስተ መና

ህብስተ መና ይወርዳል ሲሉኝ፣
ከሰማይ፤
እንዲያው ወሬ ይመስለኝ ነበር፣
እውነትነቱ ማይዳሰስ፣
እውነትነቱ ማይታይ።

ግን አየሁት ሲወርድ፣
ዘመን ያመጣው ነው ተብሎ፤
የሚገመጥ ዳቦ ባይሆንም፣
በእግረ ሰፊ ሱሪ ተመስሎ።

፻፩

# ባለሁበት የማልገኝ

ብዙ ማድረግ ስመኝ፣
በሀሳብ ባህር ውስጥ ስዋኝ፣
ከፊቴ ድቅን ይላል፣
        ረጅም እድሜ እንደሌለኝ፡፡

«ራሴን ከቻልኩ ጀምሮ፣
ሞት ጥላውን እስኪያጠላብኝ፣
መጣር ብቻ ነው ፋንታዬ፣
        መስራት ብቻ ነው ያለብኝ፡፡

ጊዜው አጠረም ረዘመ፣
        አየሩን የተነፈስኩበት፣
ችግሬ ለዚያ ብቻ ነው፣
        የኔነቴ ትርጉም ስላለበት፡፡

እድሜዬየ ባጭሩ ቢቀር፣
        ሳምባዬ መተንፈስ ቢሳነው፣
ልቤ ትርታ ሰልችቶት፣
        ማረፍ መዝናናቱ ቢያምረው፣
ምናለ!

እስከዚያው እኖራለሁ፣
የምወደውን አደርጋለሁ፣
የምችለውን እሰራለሁ፡፡

ብዙ ጊዜ ቢኖር፣
        ቢያገኝ እድሜ ያልታለመ፣

ሰው እንደሁ ምኞቱን አያቆም፣
ብሎ ዘመኔ ረዘመ፡፡»

ምንኛ የታደለ ነው፣
ይህን የሚል ፍጡር፤
ስለዛሬ የሚያስብ፣
ዛሬን ብቻ ሚመረምር፡፡

እኔ ግን ያልታደልኩ ነኝ፣
መጨረሻዬን ሳሰላስል፣
ባለሁበት የማልገኝ፡፡

# ከእውነት ይሆን ስህተቱ?

የትኛው ነው እውነቱ?
          የኔ ወይስ የመስተዋቱ?
ማንኛችን ነን እውነት?
          ማንኛችን ነን እኔ?
ኧረ ፍቱልኝ ይህን ቅኔ።

ከእውነት ይሆን ስህተቱ?
ወይስ ከመስተዋቱ?

ማንኛችን ነን ቁዋሚ?
          ማንኛችንን ነን ቅዠት?
ሁለታችንም ምስል?
          ወይስ አንድ ላይ ፍጥረት?

# ኪነት

## ሙዚቃ

ንፁህ ውበት፣
 የውበት መገለጫ፣
የኑረታው ማረጋገጫ፡፡

ውበትነቱን አድንቆ፣
ርዝራዡን ትቶ፣
የሰው ልጅ የተቀበለው፣
 የሚዳሰስ አካል አድርጎ፣
የሚጨበጥ እቃ፣
ሙዚቃ፡፡

የታደለ፣
የውበት አካል፣ አምሳል፣
 ውበት ብቻ የሆነ፡፡

# ኪነት

## ስእል

እንደ ሙዚቃም ባይሆን ንፅህናው፣
ውበቱ፤
ተሞክርዋል፣
ሙከራውም ተሳክትዋል፣
መለየቱ፣
የስእልን ውበት ከመልእክቱ፡፡

## ስነ ፅሁፍ

ያልታደለ፣
የውበት አካል ሆኖ፣
        ውበት ብቻ ያልሆነ፡፡

የመልእክት ተገዥ፣
        ነፃነቱን የተገፈፈ፣
ውበትነቱ ባያጣላም፣
        ንፁህነቱን የተዘረፈ፡፡

ያልታደለ፣
የውበት አካል ሆኖ፣
        ውበት ብቻ ያልሆነ፡፡

# አባሪ

፯ መግቢያ፡ ሀዲስ አለማየሁ፤ ፍቅር እከመቃብር፤ ፲፱፻፷፭ አም፤ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

፱ መግቢያ፡ Call of Ethiopia, Page 184. Rampersad, A. & Roessel, D. The Collected Poems of Langston Hughes 1994, Alfred A. Knopf Inc.

፲፫ ሚሲስ ፎርድ፡ የልእልት ዘነበ ወርቅ ትምህርት ቤት ባለቤት ነበሩ፡፡ ይህ ግጥም መጀመሪያ በ Ethiopian Register (EtR) ላይ ታትምዋል፡፡

፲፯ መስተዋት፡ ገዝፍ=Matter ዋዘፎ=Mass ውዝፈት=Inertia ፍትሸት=Experiment ህስበት=Imaginary ገን=Perpendicular ዘዌ=Angle ስነ-በሲር=Optics ፊዚካ=Physics ፈርጅ=Component

፳፫ የተረበሸ ፀጥታ፡ ክትለት=Effect እርግብጋቦ=Vibration እርግብግቢት=Vibrator

፳፬ ላኮታ፡ ኮሎምቢያ ሚዙሪ፣ ዘጠነኛው መንገድ ላይ የሚገኝ፣ የኢትዮጵያ ቡና የሚሸጥበት ሱቅ ነው፡፡ ይህ ግጥም መጀመሪያ በ EtR ላይ ታትምዋል፡፡

፳፭ የትምህርት ክፋቱ፡ እኩልታ=Equation መደበል=To integrate ስነ ዛመዶ=Relativity መቀምር=Computer

፳፯ ጣእም፡ ገዳመ-ጥበብ= University

፴፩ መቀመቅ፡ እና «እርሻ» መሰረታቸው አንድ ነው፡፡ «እርሻ» ጠፍቶ ስለነበር፣ «መቀመቅ» በእርሱ ፋንታ የተፃፈ ግጥም ነበር፡፡ በሁለቱ መሀል ግን፣ ለራሴም የገረሙኝ ልዩነቶች አሉ፡፡

ለምሳሌ፡ «እርሻ» ውስጥ እሳቱን ያነደደልኝ ሌላ ሰው (ምናልባት አሸከር) ሲሆን፣ «መቀመቅ» ውስጥ ግን ራሴው ነኝ። ነገሩ ምኞት ቢሆንም ከእውነታ መራቅ ምንኛ ያስቸግራል።

፴፱ መንግስቱ ሀይለ ማርያም፡ ምስራቅ ጀርመን ለጉብኝት ሄዶ፣ መፈንቅለ መንግስት የተሞከረ እለት የተፃፈ ነው።

፵ ደስታ፡ የ ቀኃሥ ቴአትር ዳንኪረኛ ነበረች።

፵፫ አዋሽ፡ ሂውስተን፣ ቴክሳስ የሚገኝ፣ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት።

፶፩ የጎሳ ዴሞክራሲ፡ የዚህ ግጥም መነሻ ሀሳቡ ዶክተር ጥላሁን ስንሻው EEDN የተባለ የኢትዮጵያውያን የኮምፒውተር መገናኛ ላይ፣«Electronic Conflict Resolution?!» በሚል ርእስ ከፃፈው አስተያዬት የተወሰደ ነው።

፶፫ ይገርመኛል፡ እፍጋት=Density ማእከል=Medium

፶፱ ይላላ ደነቦ፡ My People, Page 36. Rampersad, A. & Roessel, D. The Collected Poems of Langston Hughes 1994, Alfred A. Knopf Inc. ይህ ግጥም መጀመሪያ በ EtR ላይ ታትምዋል።

፷፪ አማራ፡ የተፃፈው ከ ፳፭ አመት በፊት ነበር። «የሌሎች ሁሉ ግፍ ተደምሮ» የሚለው ሀረግ፣ የ፪ ባለስልጣኖች ስም ነበረበት። ከዚያ በሁዋላ የመጡትን፣ አሁንም ያሉትን ገዥዎቻችንን ስመለከት፣ የነዚያን ባለስልጣኖች ስም በመጥፎ ማንሳቱ ቅንጦት ስለመሰለኝ፣ ትቼዋለሁ።

፺፩ ውበት፡ ይቻልታ=Possibility.

፻ ውሸት፡ የአፖሎ ፲፩ ግልገል መንኮራኩር ጨረቃን የለቀቀ እለት የተፃፈ።